# በፊታችን የተገለጠው
# ኃያል አምላክ

ወደ እናንተ ለማስተላለፍ፡ ያዘጋጀኋቸው ጥቂት ቅዱሳን ቃላት ጽፌአለሁና፡ እግዚአብሔር ጥቂቷ ጥረታችንን እንደሚባርክ አምናለሁ።

2 ብዙ ሰዎች፡ ለምን ሞኞች እና ጨኸታሞች ሆናችሁ ብለው ሰለኛ ይገረማሉ። ታውቃላችሁ፡ ይህ አይነት ኮንቬንሽን—ሰዎች ከሚያዩት አይነት—ትንሽ ወጣ ያለ ነው። ሌሎቹ፡ በተለምዶ፡ ጸጥ-ረጭ-እና ደረቅ ቅርጽ ያላቸው ናቸው። ወደኛ ኮንቬንሽኖች ስንመጣ ግን፣ እንደመታደል ሆኖ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ዓመታት አስቆጥሯል፡ መጥተን ምን ማድረግ እንደሚባን እንኳን አናውቅም። በቃ መጥተን እራሳችንን እንሰጣለን። ማድረግ የምንችለው ነገር ይህ ብቻ ነው። ቀሪው እግዚአብሔር ያደርገዋል። ስለዚህ ይህ ነገር ስራቸውን በልዩ-ሁኔታ የሚተውኑ ሰዎች አድርጎናል።

3 በቀደም፡ አንዱ "ታውቃለህ፡ በእውነት እናንተ ሰዎች ግን ቂሎች ናችሁ፡" አለኝ።

እኔም "አዎን፡ ነን ብዬ—እገምታለሁ፡" አልኩት።

4 አንድ ኮንቬንሽን ላይ አስታውሳለሁ። አንድ ጊዜ ወንድም ትሮይ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ተጠመቅኩኝ ስለሚል አንድ ጀርመናዊ ሰው ነገረኝ። እና በማግሥቱ ይሠራበት በነበረው ሱቅ ውስጥ፡ እጁን ዘርግቶ ጌታን ያመሰግናል፡ ክፉኛ በልሳን ይናገራል፡ አያቆምም። በመጨረሻም፡ አለቃው መጣና አለው፡ "ሄኒ፣ ምን ገጠመህ? "

5 እርሱም፡ "ኡህ፡ ዳንኩኝ'ኮ።" "ልቤ በደስታ ተሞልቶ ይፈሳል፡" አለው።

6 "አይ፡ ማዶ ላይ ካሉት እብዶች ጋር ተገናኝተህ ሳይሆን አይቀርም፡" አለው።

7 እርሱም፡- "አዎን፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን!" "ስለ እብዶቹ ጌታን አመሰግናለሁ፡" አለው። እርሱም አለው—እንዲህ አለ፦ "አውቶሞቢሉን ይዘህ፡ ወደ መንገድ ውረድ።" "ብሎኖቹን ሁሉ ብትፈታታው፡ 'ከቁራሌ' ክምር በቀር ምንም አይቀርልህም፡" አለው። እውነት ነው... እውነት'ኮ ነው፡ ታውቃላችሁ።

8 አንድ ቀን፡ በካሊፎርኒያ፡ በሎስ አንጀለስ ጎዳናዎች ላይ ስወርድ፣ ደረቱ ላይ ምልክት ያንጠለጠለ ሰው አየሁ፡ እና **በዚህ** በኩል። ሰውዬው "ለክርስቶስ ሞኝ ነኝ፡" ይላል። ሰው ሁሉ እሱን ያያል። ካለፈ በኋላም፡ ወደ ኋላቸው እየዞሩ ሲመለከቱት አስተዋልኩና። እኔም እንደሌሎቹ ልዙር አልኩኝ። እና ከኋላው... ጀርባው ላይ፡ "አንተስ የማን ሞኝ ነህ? " ይላል፤ አዎ። እኛ ሁላችንም፡ አንዱ ለሌላው፡ ሞኞች ነን፡ ታውቃላችሁ።

9 የሆነ ነገር መጥቶ እንግዳ እስከሚያደርገው ድረስ ግን፡ ታውቃላችሁ፡ ሰዎች ሁሉ ይሄ'ማ የሆነ ነገር ነው፡ ብለው እስኪያስቡ ድረስ ዓለም እጅግ

ይሰላችበታል። ብዙ ጊዜም እግዚአብሔር ህዝቡን እንደገና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ለመመለስ ያልተለመደ ነገር ያደርጋል።

10 ኖህ ይኖርበት ለነበረው ለሳይንሳዊው ዘመን—እብድ ነበረ ብዬ አስባለሁ፡ ምክንያቱ ሰማዩ ውኃ እንዳልነበረው መርምረው አረጋግጠዋል። እግዚአብሔር ግን ይኖራል ብሏል። ስለዚህ፡ ኖህ፡ ይሄን እምኖ በመሰበኩ፡ እብድ ተባለ።

11 ሙሴም ወደ ግብጽ በወረደ ጊዜ፡ በፈርኦን ፊት፡ እብድ እንደነበረ—አስባለሁ። ነገር ግን አስታውሱ፡ ፈርኦን ራሱ፡ ለሙሴ እብድ ነበረ። ስለዚህ... ይሄን እንገነዘባለን።

12 ኢየሱስም እንደ መናፍቅ ይቆጠር ነበር። በትክክል። ማርቲን ሉተር፡ ለካቶሊክ ቤተክርስትያን እንደ እብድ ነበር። ጆን ዌስሊም፡ ለእንግሊካን እብድ ነበር። እንግዲህ፡ ይህ ጊዜም፡ የአንደኛው እብድ—ዘመን ነው። አይመስላችሁም? ብሎን ከመታሰሩ፡ በፊት፡ ግን፡ የሚታሰርበት ዘንግ፡ መኖሩ ግድ ነው።

13 ስለዚህ... ኖህን፡ እንደምታውቁት፡ ለራሱ፡ ብሎን ሲሆን፡ ብሎን በማዞር፡ ዘንጉን እየጎተተ፡ አንድ ላይ በመጎተት፡ አንዱ ከሌላው ነገር ጋር አጠበቀው። ስለዚህ ኖህ፡ ብሎን በመሆኑ፡ የሚያምኑ ሁሉ ከፍርድ እየሳበ፡ ወደ መርከብ እንዲገቡ አድርጓል።

14 ሙሴም፡ ብሎን በመሆኑ፡ ቤተ ክርስትያንን ከግብጽ እንዳወጣት፡ አውቀናል። ትክክል ነው።

15 አሁንም ሙሽራይቱን ከቤተ ክርስቲያን ሰቦ የሚያወጣ ብሎን፡ ያስፈልገናል። እጅግ ለየት ያለ ሞኞች ዓይነት ሰዎች ነንና፡ እኛም አንድ ነገር፡ አንድ ሰው ያስፈልገናል። ጌታ ቢፈቅድ፡ በዚህ ምሽት፡ ይሄን ጉዳይ በተመለከተ ጥቂት ቅዱስ ቃል እንብቤላችሁ፡ ጥቂት ነገሮችም ተናግሬ፡ ለምን ሞኞች ሰዎች እንደሆንን ላሳያችሁ እሞክራለሁ፡ ብዬ አስቤአለሁ።

16 ሁላችንም ክርመጽሐፍ ቅዱስ፡ ፊልጵስዮስ ሁለተኛው ምዕራፍ እንከፍታለን፡ ከ1-8፡ በመቀጠል ሁለተኛው ቆሮንጦስ 3፡6። የእግዚአብሔርን ቃል እንደምናምነው ሁሉ፡ እናንብበው።

17 ከማንበባችን በፊት፡ አንገታችንን ለጸሎት ዝቅ እናድርግ።

18 ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ፡ በዚህ ዘመን በመኖራችን፡ አሁን እየተፈጸሙ ያሉ ነገሮች ማየት በመቻላችን፣ እና ኢየሱስ ለገዛ ቤተ ክርስትያኑ የሚመጣላት ጊዜ፡ በደጅ መቅረቡ በማወቃችን፣ በእውነት የታደሉ ሰዎች ነን። ኦህ፡ ጌታ ሆይ፡ ልባችንን በደስታ ይሞላዋል! ዛሬ ምሽት፡ እኛ ገጾችን ስንገልጥ፡ ከተጻፈው ዘንድ የቃሉ ይዘት እንድትሰጠን እንጸልያለን። መንፈስ ቅዱስም መልካም የሆነውን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኛ ነገር ለልባችን ይግለጽልን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

19 አያችሁ፡ አንድ ነገር እጠይቃችኋለሁ ብዬ አስቤአለሁ። ብ—ብዙ ጊዜ እንግዳ ነገሮችን እጠይቃለሁ፡ እና እንግዳ ነገር እንደማልጠይቅ ተስፋ አደርጋለሁ። ለሰንደቅ አላማ ክብር ስንሰጥ፡ ሁላችንም እንቆማለን። እኛ ቆመን፡ ሰንድቅ አላማው—ያልፋል፡ ይህም፡ ማድረግም አለብን። ሰላምታ ለመስጠት፡

እንቆማለንና። ፈቃደኞች ከሆናችሁ፡ ከሁለተኛው ቆሮንጦስ 3፡6 ቃል ሰናነብ፡ ሁላችንም በእግሮቻችን እንቁም።

**እርሱም... ደግሞ በመንፈስ እንጂ፡ በፊደል ለማይሆን፡ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።**

**ዳሩ ግን—ስለዚያ ሰለ ተሻረው፡ የእስራኤል ልጆች** ሰለ ፊቱ **ክብር የሙሴን ፊት፡ ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ በድንጋዮች ላይ በፊደላት የተቀረጸ፡ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፡**

**የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም?**

**የኵነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ፡** ይልቅ **የጽድቅ አገልግሎት በክብር** አብዝቶ **ይበልጣልና።**

**ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር** ምክንያት፡ **በዚህ ነገር ክብሩን አጥቶአልና።**

**ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ፡ ጸንቶ የሚኖረውማ** እጅግ... ይልቅ **በክብር ሆኖአልና።**

**እንግዲህ እንዲህ** ያለ **ተስፋ ካለን፡ እጅግ ገልጠን እንናገራለን።**

**የዚያንም ይሻር የነበረውን፡ መጨረሻ ትኩር ብለው፡ የእስራኤል ልጆች እንዳይመለከቱ በፊቱ መጋረጃ እንዳደረገ እንደ ሙሴ አይደለንም።**

**ነገር ግን አሳባቸው ደነዘዘ፤ ብሉይ ኪዳን ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከ ዛሬ ድረስ ይኖራልና፤ በክርስቶስ ብቻ የተሻረ ነውና።**

**ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ፡ የሙሴ መጻሕፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ፡ ያ መጋረጃ በልባቸው ይኖራል።**

**ወደ ጌታ ግን** ዘወር ባለ **ጊዜ ሁሉ፡ መጋረጃው ይወሰዳል።** አይ...

**ጌታ ግን መንፈስ ነው፡ የጌታም መንፈስ ባለበት፡ በዚያ አርነት አለ።**

**እኛም ሁላችን፡ በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን፡** ወደ ምን እንለወጣለን **መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።**

20 በፊልጵስዩስ 2፡ ይህን ከ1ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ እስከ 8ኛው ቁጥር ድረስ፡ እናነባለን።

**በ—በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን ይሁንላችሁ፡ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፡... የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፡** ምሕረትና **ርኅራኄ ቢሆኑ፡**

**በአንድ አሳብ ተስማሙ፡** እና **በአንድ ፍቅር በአንድም ልብ፡** በአንድም **አሳብ፡ ደስታዬን ፈጽሙልኝ።**

**በክርክር ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው** ከራሱ ይልቅ **እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር።**

**እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፡ ለባልንጀራው... ደግሞ እንጂ።**

**በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ፡ በእናንተ** ዘንድ ደግሞ **ይሁን፤**

**እርሱ፡ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ፡ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፤**

**ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፡ በሰውም ምሳሌ ሆኖ፡ ራሱን** ባዶ **አደረገ፤**

**በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ፡ ራሱን አዋረደ፡ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ፡ የታዘዘ ሆነ።**

21 እንጸልይ።

22 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ከቅዱስ ጽሁፍ የተነበበው፡ ይህ ታላቅ ቃል፣ ከዚህ ሰንሄድ፡ ከኤማሁስ ተጉዘው እንደተመለሱ መንገደኞች፡ "በመንገድ ሲያናግረን ልባችን ይነድብን አልነበረምን?" እንዳሉ በልባችን እውነት አድርገው፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

23 እንግዲህ፡ ጽሑፉ እንግዳ ቢሆንም፡ ለዚህ ወቅት የሚመጥን እንደሆነ ግን አስባለሁ። **በፊታችን የተገለጠው ኃያል አምላክ፡** በሚል ርዕስ እናገራለሁ።

24 እንግዲህ ሰው ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ፡ ከየት እንደመጣ፣ ለምን ምክንያት እንደመጣ፣ ወዴት እንደሚሄድ፣ ለማወቅ የመፈለግ ረሐብ፡ በሰው ልብ ዘወትር ነበረ። ይሄን መልስ የሚመልስ አካል ግን አንድ ነው፡ እሱም ወደዚህ ያመጣው አካል ነው። ሰው ሁሌም እግዚአብሔርን ማየት ይፈልጋል።

25 በብሉይ ኪዳን ዘመን፡ እግዚአብሔር እራሱን ሰዎች ሸፍኖ እንደነበረ እናገኛለን። እግዚአብሔር በሰዎች ዘንድ እጅግ ባልተለመደ መልኩ ይሰራል። እራሱን ከማያምኑ ደብቆ፡ እራሱን ለአማኞች ይገልጣል። እንዲህ ያደረገ እግዚአብሔር ራሱ ነው። እነዚህን ነገሮች፡ ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውሮ፡ ለሚማሩ እና ለሕፃናት፡ ስለገለጠላቸው ኢየሱስ አብን አመሰግኗል። ስለዚህ እግዚአብሔር፡ በባሕሪው ፈጽሞ እንደማይለወጥ፡ አሠራሩም አንድ ዓይነት ሆኖ እናገኘዋለን። ሚልክያስ 3 ላይ፦ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ አልለወጥምም፡" ብሏል። ስለዚህ እሱ፡ ሁል ጊዜ በተመሳሳይ መርህ ይሰራል።

26 አሁን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊው ከሚባሉት አንዱን መጽሐፍ እንይ። በዘመኑ ከነበሩት እጅግ ጻድቅ ሰዎች፡ አንዱ የነበረው ኢዮብ፡ በእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ሰው፣ እግዚአብሔር፦ "በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ የለም፡" ብሎ እስኪመሰክር ድረስ፡ ያገለገለ፡ ክቡር፡ የተከበረ አገልጋይ ነበር። አንድ

ቀን ግን... እግዚአብሔርን ለማየት፡ ተመኘ። እግዚአብሔር መኖሩን ስላወቀ፡ እንዲያየው ፈለገ፡ ወይም፡ ደግሞ፡ ቤቱ ድረስ ሄዶ፡ አንኳክቶ፦ “ካንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ።” እርስ በርሳችን እንደምንነጋገረው፡ ከእርሱ ጋር፡ ቁጭ ብሎ መነጋገር ፈለገ።

27 እኛ ሁላችንም እንደምንግባባው አይነት። ወደዚህ ኮንቬንሽን የመጣነው ለዚህ ነው፡ አንድ ላይ ስንሆን—ሐሳቦቻችንን እንናጋራለን። አንዳችን ከሌላው ጋር—ስንነጋገር፡ አንዳችን ከሌላው ጋር፡ በደንብ እንድንግባባ ይረዳናል። አገልጋዮች ያደርጉታል። በተለያየ የህይወት ጎዳና የሚኖሩ ሰዎች፡ ስለ ነገሮች ይግባባሉ።

28 እዮብም፡ እግዚአብሔር ለእሱ እጅግ እውነት ስለሆነበት፡ ወደ በሩ ቀርቦ፡ ማንኳኳት ይችል እንደሆነ፡ እና ከእርሱ ጋር፣ መነጋገር—ይችል እንደሆነ— መመርመር ፈለገ።

29 እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ሲነጋገር አይተናል፡ ይሁን እንጂ እራሱን ሸፍኖ ነበር። በአውሎ ነፋስ ተሸፍኖ ነበር። እዮብ ሆይ፡ እንደ ሰው አነጋግርሃለሁና፡ ወገብህን ታጠቅ ብሎ ነገረው። በዐውሎ ነፋስም ወረደ—ኢዮብንም ተናገረው። ለኢዮብም በዐውሎ ነፋስ ታወቀ፡ ነገር ግን በትክክል አላየውም። በዛፎቹ ውስጥ ነፋሱ ሲነፍስ እና ሲዞር ብቻ ሰማው። ድምፁም ከዐውሎ ነፋስ ይወጣል፣ እግዚአብሔር ግን በዐውሎ ነፋስ ተሸፍኖ ነበር።

30 በአፍሪካ፡ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ፡ **እሞያህ፡** የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ፡ “የማይታይ ኃይል፡” ማለት ነው።

31 እናም ይህ የማይታየው ኃይል፡ በዐውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ፡ የሚሰማ ድምጽ ነበረው። ለኢዮብ ተናገረ፡ መልክ ግን ፈጽሞ አላየም። እሱ ግን፡ በዐውሎ ነፋስ፡ ተጋርዶበት ነበር።

32 የብሉይ ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር ከመረጣቸው፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ነቢያት አንዱ የነበረው፡ አስቀድሞ ከወሰናቸው አገልጋዮች፡ ከተመረጡት፡ አንዱ የነበረው ሙሴ፡ እርሱን ሊያየው እንደፈለገ እናያለን። ወደ እርሱ በጣም ቀርቦ፣ ታላቅ ሚስጢራዊ እጁ በፊቱ ሲሄድ እና እግዚአብሔር ብቻ ሊሰራ የሚችለውን ሲሰራ አይቷል። አንድ ቀን ሊያየው ወደደ፡ እግዚአብሔርም “ሂድ፡ በዓለቱ ላይ ቁም፡” አለው።

33 ሙሴም በዓለት ላይ ቆሞ፡ ሲያልፍ አየው። ጀርባውን ብቻ አየ። እርሱም “ሰውን ይመስላል፡ የሰው ጀርባ ይመስላል፡” አለ። ሆኖም፡ የእግዚአብሔርን መጋረጃ ብቻ አየ እንጂ። አምላክን አላየም።

34 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ “እግዚአብሔርን በማንኛውም ጊዜ ያየው አንድ ሰንኳ የለም፡ የአብ አንድያ ልጅ ግን ገለጠው።” ስለዚህ፡ ሙሴም፡ እንደተሸፈነ ሰው፡ ሆኖ አየው። የብሉይ ኪዳኑ ያህዌ የአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ሆኖ አናገኘዋለን።

35 እ—እዚህ ጋር፡ እንደ ዶክተር ስኮፊልድ፡ ቃሉ፡ “ቅርጽ” እንደሚቀይር እንረዳለን። **ኤን ሞርፌ፡** የሚለውን ቃል፡ በግሪክ ቋንቋ “የማይታየው የሚታይ ሆነ” ማለት እንደሆነ እንረዳለን። አንድ ነገር ነው... እናየውም። ህልውናውን

እናውቃለን... ግን አናየውም፡ ህያው መሆኑ ግን እናውቃለን። **ከኤን ሞርፌ፡** መልኩ ሲቀይር፡ ይህ ማለት ከመለኮት ወደ ተፈጥሮ ተቀየረ ማለት ነው።

36 ጭምብሉን ብቻ ቀየረ ማለት ነው፡ በሌላ አባባል፡ እንደ ድራማ ነው። እየተወነ ነበር። በግሪክ ደግሞ፡ ጭምብላቸውን ሲቀይሩ፡ ምናልባት አንድ ሰው-... አንድ ተዋናይ የተለያየ ገጸ ባህርይ ውሰጥ ሊተውን ይችላል።

37 እዚያ ጋር ያለችው፡ ሴት ልጄ፡ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታቸው፡ ተውኔት—አዘጋጅተው ነበር። ያ የማውቀው ልጅ፡ አራት ገጸ ባህርያቶችን ተጫውቷል፡ ሌላ ገጸ ባህሪን ለመምሰል፡ ከመድረክ ጀርባ ሄዶ፡ ጭምብሉን አውልቆ—ራሱን ይለውጣል።

38 እንግዲህ፡ መሲሁ ማን እንደሚሆን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን አይታችሁ፣ ከኢየሱስ ሕይወት ጋር በማነጻጸር፣ ኢየሱስ ማን እንደነበረ በትክክል ማወቅ ትችላላችሁ። ተራ ሰው አልነበረም። እርሱ አምላክ ነበር፡ **ኤን ሞርፌ**። ከ—ከመለኮታዊ መልክ ወደ ተፈጥሯዊ የሰው መልክ ተቀየረ። ሆኖም ግን፡ በሥጋ የተገለጠ፣ በሰው የተከደነ፣ በሥጋ መጋረጃ የተጋረደ አምላክ ነበር።

ብሉይ ኪዳንን ተመልከቱ።

39 ዛሬ ማታ፡ ከተለያየ ክፍለ—ዓለም—ለመጡ ለድብልቅ-ጉባኤ እየተናገርኩ እንዳለ አውቃለሁ። ምን—ምን እየሰራን ነው? እኛ—ማንና ምንድን ነን? ወዴት እየተጓዝን ነን? አንድ ነገር ለማወቅ ተሰብሰበናል። ምን እየተደረገ ነው? ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው?

40 አሁን፡ እዚህጋ፡ አይሁዳውያን ወንዶችና ሴቶች ሆይ፡ ባለፉት ዘመናት—በቤተ—መቅደስ የነበሩ፡ ራቢዎች፡ በትውፊቶቻቸው ፈንታ፡ መጽሀፍ ቅዱስን፡ እና ትንቢቶችን፡ ቢመረምሩ ኖሮ፡ ኢየሱስ ማን እንደሆነ ባወቁ ነበር። በፍፁም ብዔል ዜቡል ብለው አይጠሩትም ነበር። ብበፍጹም ባልሰቀሉት ነበር። ይሁን እንጂ፡ ተውኔቱ መፈጸም ነበረበት። የድራማው አካል ነውና። ስለዚህ ለዚህ ጉዳይ፡ ታወሩ።

41 ብዙዎቻችሁ ወንዶች፡ ሴቶች፡ እዚህ ምሽት፡ ምናልባት እኩዮቼ ናችሁ ወይም ትበልጡኛላችሁ። ከብዙ ዓመታት በፊት፡ እዚህ አሜሪካ ውሰጥ፡ ታስታውሳላችሁ... ቻይናውያን... እዚህ የተዋወቀን፡ ወንድሜ፡ ሳነጋግረው እንዴት እንደነበሩ ትዝ አለኝ። ስራቸው ሲሰሩ... እንግሊዘኛ መናገር አይችሉም ነበር፡ እና ላውንደሪ—ይሰሩ ነበር። ልብሳችሁን ለማሳጠብ፡ ወደ ላውንደሪው ስትሄዱ። ቻይናዊው—የላውንደሪ ሰራተኛው አንድ ምልክት ይዞ ይመጣና፡ በልዩ መልኩ ይቀደዋል። እናንተ የምልክቱን ግማሽ ትወሰዳላችሁ፡ እሱም ቀሪውን ይይዛል። ንብረታችሁን ለመውሰድ በተመለሳችሁ ጊዜ፡ የሁለቱም ወረቀቶች ጫፍ መግጠም አለባቸው። በትክክለኛ መልክ ካልገጠሙ ግን... በምንም መልኩ ማስመሰል አትችሉም፡ ምክንያቱ ግማሹን እናንተ ሌላኛውም እሱ ይዛችሁታል። ከተመሳሰለ... ንብረታችሁን መውሰድ ትችላላችሁ። የውሉን ሁለተኛው አካል ከገጠመላችሁ፡ የእናንተ የሆነውን መውሰድ ትችላላችሁ።

42 እኛም የውሉ ሁለተኛው ክፍል ከያዝን፡ ዛሬም፡ ያው ነው። ያኔ ኢየሱስ በተባለው ሰው ውሰጥ፡ የኖረው እግዚአብሔር፡ ልጁን በቀራንዮ ለሁለት ከፍሎ፡ ሥጋውን ለመሥዋዕት ወደላይ፡ መንፈሱን ግን ወደ እኛ አወረደ። ዛሬም ያው አምላክ፡ በመንፈስ ቅዱስ መልክ ተሸፍኖ ይገኛል። እነዚህ ሁለቱ አካላት

ከገጠሙ፡ ከዚያ በኋላ የውሉ አካል ናችሁ። እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ፡ ለሰዎች በተሻለ መንገድ ይገለጥላቸው ዘንድ፡ ይህን አደረገ።

43 ከተወሰኑ ዓመታት በፊት አንድ ታሪክ እያነበብኩ ነበር። እናም በዚህ ታሪክ ውስጥ አንድ ታላቅ፡ የተከበረ ንጉስ አለ... ስሙን እረስቼዋለሁ። ታሪኩን እናገራለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር። በርግጥ፡ ልብ ወለድ ነው፡ ቢሆንም አሁን መናገር ወደ ፈለግነው ዳራ የሚመራን ነው። ንጉሱ፡ እጅግ የከበረ ንጉስ ነበርና፡ በግዛቱ ስር ያሉትን ሁሉ በጣም ይወዳቸው ነበር፡ የፍቅሩ ብዛት፡ አንድ ቀን፡ በመኳንንቶች—እና በጠባቂዎቹ ፊት፡ እንዲህ አላቸው፡- "ከዛሬ ጀምሮ፡ ለብዙ ዓመታት፡ አታዩኝም።"

44 ጠባቂዎቹና መኳንንቶቹም አሉት፡- "ቸር ንጉስ ሆይ፡ ለምን እንዲህ ትላለህ? መጻተኛ ለመሆን፡ ወደ ሌላ ሀገር፡ ወደ ሌላ ቦታ ትሄዳለህን? "

45 እርሱም አላቸው፡- "አይደለም። የትም አልሄድም፡ እዚሁ ነኝ።" አላቸው፡- "በህዝቤ መካከል ለመሆን እወጣለሁ። ገበሬ እሆናለሁ። ከዛፍ ቆራጮች ጋር ዛፍ እቆርጣለሁ። ከአራሾች ጋር—መሬቱን አርሳለሁ። ወይን ከሚቆርጡት ጋር ወይን ቆራጭ እሆናለሁ። ከሚያደርጉት ነገር ጋር በደንብ ለመተዋወቅ፡ እኔም ከነርሱ ጋር አንዱ እሆናለሁ። እወዳቸዋለሁ። እና በግሌ ከእነሱ ጋር የበለጠ መተዋወቅ እፈልጋለሁ። እነርሱ ግን አያውቁኝም። ይሁን እንጂ፡ በዚያ መልኩ፡ አብሬ መሆን እፈልጋለሁ አላቸው።"

46 በማግሥቱም፡ ሹማምንቱ፡ እና በቤተ መንግሥት ውስጥ የነበሩት፡ ሰዎች ሁሉ ሲያዩ፡ አክሊሉን አውርዶ፡ ዙፋኑ ላይ፡ ወንበሩ ላይ አስቀምጦታል፤ መጎናጸፍያውን አውልቆ፡ የገበሬ ልብሰ ለብሶ፡ በተራው ህዝብ መካከል ተቀላቅሏል።

አሁን፡ በዚህ ትንሽ ታሪክ ውስጥ፡ ስለ እግዚአብሔር እንማራለን።

47 ንጉሡንም "ንጉስ ሆይ፡ እንፈልግሃለን። እንወድሃለን። እኛ—ንጉሥ ሆነህ እንድትቀጥል እንፈልግሃለን፡" አሉት። እርሱ ግን እነሱን የበለጠ ለማወቅ፡ እሱንም ትክክለኛ ማንነቱን፡ የበለጠ እንዲያውቁት ወዶ፡ ከነሱ እንደ አንዱ መሆን ፈለገ። ማን እንደሆነ እራሱን በእርግጥ ሊያሳያቸው ወደደ።

48 እግዚአብሔርም ያደረገው ይህንኑ ነው። እንደ እኛ እንዲሆን፡ መከራን ይቀበል ዘንድ፡ ያሕዌ አምላክ ከመሆን፡ ራሱን—ለወጠ፡ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፡ የሞት መውጊያው ምን እንደሆነ ሊያውቅ፡ የሞት ፍርድ በራሱ ላይ ይወሰድ ዘንድ ነው። አክሊሉን እና—መጎናጸፍያውን ወደ ጎን ትቶ፡ ከእኛ ጋር እንደ አንዱ ሆነ። ከታናናሾች—ጋር—እግር አጠበ። ከድሆች ጋር፡ በድንኳኖች ኖረ። ከድሆች ጋር፡ በጫካዎች እና—በጎዳናዎች አብሮ ተኛ። እኛን የበለጠ ያውቀን ዘንድ፡ እኛም በበለጠ እናውቀው ዘንድ፡ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።

49 አሁን፡ እኔ እንደማስበው፡ ራሱን፡ ሲለውጥ፡ ያደረገውን ነገር፡ በዚያ ውስጥ፡ እናውቃለን። አመጣጡን ካስተዋላችሁ፡ በሶስት ልጆች ስም መጣ። በሰው ልጅ፣ በእግዚአብሔር ልጅ፣ እና በዳዊት ልጅ ስም መጣ። እንደ ሰው ልጅ ሲመጣ።

50 አሁን፡ በሕዝቅኤል 2:3 ላይ፡ ይሖዋ ራሱ፡ ነብዩን፡ ማለት ሕዝቅኤልን፡ "የሰው ልጅ፡" ብሎ ይጠራዋል።

51 **የሰው ልጅ** ማለት “ነብይ” ማለት ነው። ሙሴ በዘዳግም 18፡15 የተናገረውን ለመፈጸም በዚያ መንገድ መምጣት ነበረበት፣ “አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል።” ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ በፍጹም ጠርቶ አያውቅም። ልክ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት መምጣት ስለ ነበረበት፡ ስለራሱ “የሰው ልጅ፡” በማለት ይጠራ ነበር። አያችሁ? የብሉይ ኪዳን ትንቢት እና የራሱ ባህሪ፡ አንድ አይነት እንዲሆኑ፡ የተቀደዱትን ሁለቱም ወረቀቶች ማጋጠም ነበረበት። ስለዚህም፡ መጣ፡ የሰው ልጅ፡ በዚያ መልክ መጣ።

52 ከዛ በኋላ፡ ከሞተ፣ ከተቀበረ፣ ከትንሣኤው በኋላ፣ በጴንጤቆስጤ ቀን፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሲመጣ እናየዋለን፤ ያ እግዚአብሔር፡ ያ መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ መልክ መጣ። ምን እያደረገ ነበር? ራሱን እየለወጠ፡ ራሱን በሌላው መልክ ለሕዝቡ እያሳወቀ ነበር። ማለት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ፡ ማለት መንፈስ ቅዱስ በመሆን፡ በቤት ክርስትያን ዘመናት መካከል ሊሰራ መጣ።

53 በሺው ዓመት፡ ግን፡ በዳዊት ዙፋን ላይ ይነግስ ዘንድ፡ ይቅመጥ ዘንድ፡ እንደ ዳዊት ልጅ ይመጣል። አሁን በአብ ዙፋን ላይ ነው። የዳዊት ዙፋን ይወስድ ዘንድ ይገባዋል። እንዲህም አለ፦ “እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ በአባቴም ዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፡ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።” ስለዚህ፡ እሱ፡ በሺው ዓመት፡ የዳዊት ልጅ ይሆናል። ይህ ምንድን ነው? ሁል ጊዜ፡ የአንዱ አምላክ—ጭንብል መቀያየር፡ ብቻ ነው።

እኔ፡ ለሚስቴ፡ ባል ነኝ።

54 ሲሮፊኒቃዊቷ ሴት፦ “የዳዊት ልጅ ሆይ ማረኝ።” ስትለው አስተውላችኋል? እንደው፡ በፍጹም፡ ኮሽ አላለውም፡ በጭራሽ። የዳዊት ልጅ ብላ የመጥራት ስልጣን የላትም። እንደዛ ብላ የመጥራት መብት አልነበራትም። እሱ... የዳዊት ልጅ የሚሆነው፡ ለአይሁዶች ነው። “ጌታ ሆይ፡” ብላ በጠራችው ጊዜ ግን... እነሆ መጣላት፡ ጌታዋ ነውና፡ የጠየቀችውን አገኘች።

አሁን፡ እንደው፡ እራሱን እየለወጠ ነው።

55 እኔ ራሴ፡ በገዛ ቤቴ፡ ሶስት ሰዎች ነኝ። በቤቴ ውስጥ፡ ሚስቴ በእኔ ላይ የባልዋ ባለ መብት ነች። እዛ ጋር ያለችው ልጄ ግን፡ እኔ አባትዋ ነኝ እንጂ፤ የባል መብት ከእኔ አይኖራትም። እዛ ጋር ላለው ለልጄ ልጅ፡ አያቱ ነኝ እንጂ፡ እኔን አባቴ ብሎ የመጥራት መብት የለውም። የሱ አባት ልጄ ነው እንጂ። እኔ አባቱ አይደለሁም። እኔ አያቱ ነኝ። ነገር ግን ያው አንዱ ሰው ነኝ።

56 እግዚአብሔርም፡ ወደ ትውልዱ ለመምጣት፡ ያደረገው፡ ከሕዝቡ ጋር ለመተዋወቅ የተጠቀመው፡ እራሱን በመቀያየር ነው። ዛሬ ማታ የተሰበሰብነውም፡ ይህን ለማወቅ ነው። እግዚአብሔር በዚህ ዘመን ራሱን ለዚህ ሕዝብ ማስተዋወቅ ያለበት በምን መንገድ ነው? ጭምብሉን ይለውጣል፡ ተውኔቱን ይለውጣል፡ ባህሪውን ግን አይለውጥም። ተፈጥሮውን—አይለውጠውም። ጭምብሉን፡ ከአንዱ ወደ ሌላው ብቻ ይለውጣል። ይህን የሚያደርገው ራሱን ለሰዎች ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ማን እንደ ሆነ እና ምን እንደሆነ እንዲያውቁ ነው።

57 በዕብራውያን 1 ላይ፡ እንዲህ እናነባለን፦ “እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜና፡ በብዙ ጎዳና፡ ለአባቶች በነቢያት ተናግሮ፡ በመጨረሻ ዘመን ግን፡ በልጁ በኢየሱስ በኩል ተናገረ።”

58 ኢየሱስ፡ በምድር በነበረ ጊዜ፡ “ስለ ነብያት፡” ሲናገር፦ “አማልክት ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን ‘አማልክት፡’ ናቸው ትላላችሁና። ቅዱሳት መጻሕፍትም ሊሻሩ አይችሉም፡” አላቸው። እንግዲያውስ፦ “የእግዚአብሄር ልጅ ሲሆን፡ እንዴት ትኮንኑታላችሁ? ” አያችሁ?

59 የእግዚአብሔር ቃል ምን መሆን እንዳለበት፡ ለእያንዳንዱ ዘመን ዕጣ ደርሶበታል። ኢየሱስም የትንቢቶቹ ሁሉ ፍጻሜ ነው። “በእርሱ የመለኮት ሙላት በሰጋ አደረ።” በእርሱ ዘንድ ነበርና። በዮሴፍ ዘንድ የነበረው እርሱ ነው። በኤልያስ ዘንድ የነበረው እርሱ ነው። በሙሴ ዘንድ የነበረው እርሱ ነው። በዳዊት ዘንድ የነበረው፡ የተናቀው ንጉሥ እርሱ ነበር።

60 ንጉሣቸው ሆኖ ሳለ፡ የገዛ ወገኖቹ ንቀውት ነበር። ከመኖርያው——ወጥቶ በሚሄድበት ጊዜም፡ አገዛዙን——እና፡ ሰርዓቱን የማይወድ፡ አንድ የተጠቃ፡ የማይረባ ሰው መጣና፡ ተፋበት። ጠባቂውም ሰይፉን መዘዘ፡ አለም፦ “ንጉሴ ላይ የሚተፋበት፡ የዚያን የውሻ ጭንቅላት እተወዋለሁን? ”

61 ዳዊትም በጊዜው የሚያደርገውን ነገር ምናልባት አላስተዋለም፡ ነገር ግን የተቀባ ሰው ነበርና። “ተወው። እግዚአብሔር ይህን አድርግ ብሎታል፡” አለው። ሌላው እንደ ተናቀ ንጉስ፡ ተራራ ራስ ላይ ወጥቶ ኢየሩሳሌምን አለቀሰላት።

62 ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ፡ የዳዊት ልጅ በጎዳናዎች ላይ ምራቃቸውን ተፉበት፡ አስተዋላችሁ? በተራራው ራስ ላይም፡ እንደ ተናቀ ንጉስ ኢየሩሳሌምን ቁልቁል ተመለከታት። አለቀሰላት፦ “ኢየሩሳሌም ሆይ፡ ዶሮ ጫጩቶችዋን እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፡ አንቺ ግን አልወደድሽም!”

63 ባህሪውን ፈጽሞ አልለወጠም፤ ምክንያቱም ዕብራውያን 13፡8 “እሱ ትናንትና፣ ዛሬ እስከ ዘላለም ድረስ ያው ነው፡” ብሎታልና። እግዚአብሔር እኛን ከኃጢአት ይቤዥን ዘንድ፡ ሊሞት ሥጋ ሆነ። ራሱን የለወጠው፡ ለዚህ ነው፡ ይህም——ሰው ለመሆን ነው።

64 በቅዱስ ዮሐንስ፡ 12፡20 ላይ፡ ግሪኮች ስለ እርሱ መሰማታቸውን እንመለከታለን። እሱን ለማየት ልባቸው ከተቃጠሉ በቀር፡ ስለ እርሱ የሚሰማ ማንም የለም። እነ ኢዮብ እና የቀደሙት ነቢያት ሁሉም እርሱን ለማየት ፈልገው ነበር። ስለዚህ፣ ግሪኮችም ያዩት ዘንድ መጡ። የቤተ ሳይዳ ሰው ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው “ጌታዬ፡ ኢየሱስን ማየት ፈልገናል፡” አሉት።

65 ግሪኮች ሊያዩት ፈለጉ፡ ነገር ግን እርሱ በሰውነቱ ቤተ መቅደስ ውስጥ ስለነበር ሊያዩት አልቻሉም። “እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ አለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር።” በዚህ ውስጥ እንዳየነው፡ ግሪኮች፡ እሱን ማየት አልቻሉም።

66 ኢየሱስም በኋላ የተናገራቸውን ቃላት፡ ልብ በሉ። “የስንዴ ቅንጣት መሬት ውስጥ ወድቃ፡ ካልሞተች በስተቀር፡ ብቻዋን ትቀራለች፡” አለ። በሌላ አነጋገር፡

በለውጡ፡ ያኔ በነበረበት ጭንብል ውስጥ፣ በሰው ሥጋ የተከደነ ነበርና፡ እርሱን ፈጽሞ ሊያዩት አይችሉም። ነገር ግን ይህ የሰንዴ ዘር መሬት ውስጥ ሲወድቅ፡ ያኔ ብዙ ዘሮች ያፈራል። በእርግጥ በዚያን ጊዜ የተላከው ወደ አይሁዶች ነው። ይሁን እንጂ ይህ የሰንዴ ዘር መውደቅ ነበረበት፤ እግዚአብሔርን፡ በሰው ሥጋ አድሮ፡ ከማያምኑ ተሰወረ፡ ለአማኞች ግን ተገለጠ።

67 በዮሐንስ 1 ላይ፡ "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ቃልም ሥጋ ሆነ በመካከላችንም አደረ፡ ዳሰስነው፡ የአብም አንድያ ልጁን፡ ጸጋን ተሞልቶ አየነው።" እንግዲህ በመጀመሪያ ቃል ነበረ። ቃል ማለት የተነገረ ሃሳብ ማለት ነው።

68 በመጀመሪያ፡ አምላክ እንኳ አልነበረም። በዛሬው የእንግሊዘኛ ቃል፡ **አምላክ**፡ "የሚመለክ ነገር፡" ማለት ነው። ለአእምሮ እንዴት ግራ የሚያጋባ ነው። አንድን ሰው አምላክ ማድረግ ይቻላል። ማንኛውንም ነገር አምላክ ማድረግ ትችላላችሁ።

69 በብሉይ ኪዳን ግን በዘፍጥረት 1 ላይ፡ "በመጀመሪያ **እግዚአብሔር**" ሲል፡ ኤሎሂም፡ የሚለው ቃል ተጠቅሟል። **ኤሎሂም** "ከራሱ-የሚኖር" ማለት ነው። ኤሎሂም የሚለው ቃል፡ አምላክ ከሚለው የኛ ቃል ትልቅ ልዩነት አለው። **ኤሎሂም** ማለት "ከራሱ-የሚኖር" ማለት ነው።

70 እኛ ከራሳችን-መኖር አንችልም። ሁሉን የሚችል፡ ሁሉን ቻይ፡ በሁሉም ቦታ የሚገኝ፡ ሁሉን የሚያውቅ ልንሆን አንችልም። ኤሎሂም ያንን ሁሉ ይገልጸዋል። እኛ እንደዚያ መሆን አንችልም። ፈልፍላችሁ አምላክን የምትቀርጹበት ያንን ዛፍ፡ ወይም——ህንጻው፡ ከራሱ-የሚኖር አይደለም።

71 ስለዚህ፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ ዘላለማዊ የሆነ፡ ህይወት፡ ነበረ። በእርሱ ዘንድ መገለጫዎች ነበሩት፡ መገለጫዎቹም ቃሎች ሆኑ፡ ቃልም ስጋ ሆነ። ኢየሱስ የሚዋጅ ነበር። **መዋጀት** ማለት፡ "መመለስ፡" ማለት ነው። መልሶ ማምጣት ካለበትም፡ ወደነበረበት የሚመለሰበት ቦታ መኖር ያስፈልጋል። ስለዚህ፡ እያችሁ፡ ሁሉም ሰዎች በእግዚአብሔር በመጀመሪያው ሐሳቡ ስላልነበሩ፡ ሁሉም ሰዎች በፍፁም ሊያዩት አይችሉም። እያችሁ?

72 ካህናቱን እዩአቸው። ስለራሱ ምን እንደነበረ በቃሉ በትክክል ራሱን ሲገልጽ ሲያዩት፡- "ብዔልዜቡብ ነው፡" አሉት። ባህሪያቸው ከየት እንደነበር ያሳያል። በወቅቱ ከነበረው ዘመናዊ አስተሳሰብ ውስጥ ነበሩና።

73 ያቺን ጋለሞታ ግን፡ በበሩ ላይ ባገኛት ጊዜ፡ ያደረገችውን በመንገር፡ መሲሐዊ ምልክቱን ገለጸላት። "እንዴ፡" አለችና፡ "ጌታ ሆይ፡ ነብይ እንደሆንክ እያለሁ። መሲሑ ሲመጣ፡ እነዚህን ሁሉ እንደሚነግረን፡ እናውቃለን።" የቅዱሳት መጻሕፍትን መመዘኛዎች ሁሉ አሟልቷልና እርሱን መሲሕ፡ እና የተቀባው መሆኑን አወቀችው። አይታያችሁምን? የተቀደዱ ሁለቱ ወረቀቶች አንድ ላይ ገጠሙ። እሷም፡- "መሲሑ ሲመጣ፡ እናውቃለን።"

74 እግዚአብሔር፡ እንደ ቅርጽ አውጪ፡ ይችን የደወል ድምጽ ለማግኘት፡ **ይህን** እና **ያንን** መቀላቀል ሊኖርበት ይችላል። ኢየሱስም ዘወር ብሎ፡- "ከአንቺ ጋር የምናገረው እኔ እርሱ ነኝ" ባላት ጊዜ ግን፡ "ብዔልዜቡብ" ብሎ ነገር አልነበረም። እንስራዋን ትታ፡ ወደ ከተማ ሮጠች፡ እና እንዲህ አለች፡-

“ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው፡ ኑና እዩ። እንጃ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? ” አያችሁ?

75 እሺ፡ ይህስ ምን አደረገ? የብሉይ ቃላትን—ኢየሱስ አሁን ከሚሰጣት ልምምድ ጋር በማቀላቀል፡ ምን አደረገ? መሲሑን አደረገ። ከዛስ አስተውላችኋል? ኃጢያቷ በፍጥነት ተሰረየላት፣ ምክንያቱ፡ በመጀመሪያም፣ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር አስተሳሰብ ውስጥ ስለ ነበረች፡ የምትቤዥ ነበረች። ይሖዋ፡ ምን እንደ ሆነ፡ ምን እንደ ነበረ፡ የሚገልጹ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲገለጡ ባየች ጊዜ፡ ስለዚህ ዋጀት፡ ወይም መለሳት።

76 ኢየሱስ፡ በመጣ ጊዜ፡ የኖህን መልእክት ይዞ ቢመጣ ኖሮ፡ አይሰራም ነበር። መርከብ ለመሥራት፡ እና ለመንሳፈፍ፡ አይሆንም ነበር። ኖህ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ በከፊል ነበር። ልዩ ስለነበረ በልዩ መንገድ ተወነ፡ መልእክቱ ልዩ የሆነበት ምክንያትም የተገለጠው ቃል በመሆኑ ነው።

77 ስለማይሰራለትም፡ የሙሴን መልእክት ይዞ መምጣት አይችልም ነበር። ሙሴም፡ በከፊል የተገለጠ፡ እግዚአብሔር ነበር። ለዚያ ዘመን የተገለጠው ቃል እሱ ነበር፡ ቢሆንም፡ ኢየሱስ በዚያ ሊመጣ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ መንገድ ይመጣል በፍጹም አላለም።

78 በመጣ ጊዜ ግን፡ ልክ ቃል ኪዳኑ—እንዲህ ይገለጣል ብሎ በተናገረው መልኩ፡ ተገለጠ፡ ከዚያም በእግዚአብሔር በአሳቡ ስለ ነበሩ፡ ለቤዛነት የተመደቡት ሰዎች ሁሉ አመኑት። በመጀመርያ የነበሩ መገለጫዎቹ ፡ ሊዋጁ የሚችሉ፡ ስጋ ሆኑ፡ ወደ እግዚአብሔርም ተመለሱ። “ለተቀበሉት ሁሉ ግን፡ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።” ምክንያቱ ሊዋጁ የሚችሉ ስለ ነበሩ ነው። እነኚህ ከመጀመርያ ጀምረው፡ በተነገረው ዘንድ ነበሩ።

79 እዚህ ጋር፡ ዛሬ ማታ፡ የሚቻል ከሆነ፡ ስለተነገረው የይሖዋ ሐሳብ፡ ስለ ዘመኑ መልዕክት፡ ለማስላሰል፡ ለአፍታ ያህል ቆም እናድርገው። “ዓለም ከመፈጠሩ በፊት፡” “ስማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ ተቀምጧል፡” ተብሎ ተነግሮናል። ስለዚህ በመጀመርያ እንዳልኩት፡ አንደኛው ለሌላኛው ሞኝ የምንሆንበት፡ ሁለቱ ጠርዞች መመልከት እንችላለን። እንዲያ መሆኑ ግድ ነው። ድሮም እንዲህ ነው። ከጥንት ጀምሮ እንዲሁ ነበር፡ ወደፊትም እንዲሁ ይቀጥላል። “እርሱ ቃል ነበር። ቃልም ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።”

80 አሁን፡ ያኔ... በብሉይ ኪዳን ዘመን፡ እግዚአብሔር፡ ለህዝቡ በብዙ ዓይነት መልክ፡ ከተገለጠላቸው በኋላ፡ ባረጁ የአቆስጣ ቆዳዎች በስተጀርባ እራሱን ሲሸፍን አይተነዋል። እግዚአብሔር በምሕረት ወንበሩ ላይ፡ በአቆስጣ ቆዳዎች ጀርባ ተደበቀ። ሰሎሞን፡ የጌታ ቤተ መቅደስ ሲያስመርቅ፡ እንዳየነው፡ የአቆስጣ ቆዳዎች እንደ መሸፈኛ ሆነው፡ ተዘርግተው ነበር፡ በእሳት አምድ እና በደመና አምድ ይመላለስ የነበረው እርሱ፡ በቆዳዎቹ ጀርባ ተደብቆ፡ ለተቀረው ዓለም፡ እራሱን ሰወረ። እስራኤል ግን፡ በዚያ ጀርባ እንደነበረ፡ በእምነት አወቁ። ሌላው አረማዊ ሁሉ ምንም ይበል፡ እነርሱ ግን በዚያ ውስጥ መሆኑን ያውቁት ነበር። ከማያምን ሰው ሁሉ ተሰወረ። አማኞች ግን፡ እሱ በዚያ ጀርባ መኖሩ፡ በእምነት አወቁ። ምሕረትን ሆነላቸው። እርሱም ታላቅ ምሥጢር በሆነው፡ በምህረት መክደኛው ነበር።

81 ታውቃላችሁ፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን፡ ቆዳውን አልፎ መግባት ሞት ነበር። አሁን ግን አለመግባት ሞት ሆነ። ያኔ ወደ ክብሩ መግባት ሞት ነበር። አሁን ግን ከክብሩ መራቅ ሞት ሆኗል። እውነት ነው፡ ይህ ግን፡ የብሉይ መጋረጃ፡ በተቀደደ ጊዜ፡ በቀራንዮ ላይ መጋረጃው በተቀደደ ጊዜ ሆነ። አሁን ከመገኘቱ መራቅ ሞት ነው። ያኔ ግን ወደ እርሱ መገኘት መቅረብ ሞት ነበር። አያችሁ? ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ይለወጣል፡ እናንተም በምን ዓይነት ዘመን እንደምንኖር ለማየት ቅዱስ ቃል መፈተሽ አለባችሁ።

82 ስለዚህ፡ መጋረጃው በቀራንዮ በተቀደደ ጊዜ፡ የምህረት መክደኛው በግልፅ ታየ። (ከዚያስ ምን ሆነ? በቀራንዮ ላይ ተሰቅሏል፡ ደሙም ይንጠባጠብ ነበር።) ከዓመት ወደ ዓመት፡ ደም እየወሰዱ፡ መቅደሱን እና የስርየት መክደኛው በሚያነጹበት፡ በዚያ፡ እግዚአብሔር፡ በታላቅ መብረቃዊ ኃይሉ፡ አሮጌውን የአቆሰጣ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ተረተረው፡ የስርየት መክደኛውም በግልጽ ታየ።

83 እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ለመተዋወቅ እኛም ከእርሱ ጋር ለመተዋወቅ፡ እንደ ሰው ተገኝቶ በተገለጠ ጊዜ፡ ከእኛ እንደ አንዱ በመሆን፡ እራሱ፡ ዋጋ በከፈለ ጊዜ፡ ትክክለኛው እና እውነተኛው የእግዚአብሔር በግ፡ እውነተኛውን የስርየት መክደኛ፡ በቀራንዮ ላይ በግልፅ እይታ ተሰቀለ። በዚያ የማስተሰርያው ቀን የስርየት መክደኛው በእስራኤል ሁሉ ዘንድ በግልጽ ታየ።

84 ነገር ግን፡ ወዮ፡ በዚያን ጊዜ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትውፊት ግን፡ በባሕላቸው፡ እውነተኛውን የስርየት መክደኛ ከሰዎች ሸፈኑ። ቃሉን ቢያውቁ ኖሮ ግን፡ እያንዳንዷ ቁራሽ እንደ ቻይናዊው መለያ ትሆን ነበር። የብሉይ ኪዳን ትንቢትም ይፈጸም ነበር፡ ደግሞም ተፈጽሟል። ቅዱስ ቃል የተማሩ ቢሆኑ ኖሮ፡ የስርየት መክደኛውን ማየት በቻሉ ነበር። እዚህ፡ እንደተነገረን፡ "እንደ ሙሴ፡" "እስከ ዛሬ ድረስ ተጋርደባቸዋል። በልባቸው ውስጥ ይኖራል።" አያዩትምም።

85 ይሁን እንጂ፡ መከራውን እና የሐጥያት ሰርየቱን፡ እራሱ እግዚአብሔር ነበር። በግልጽ እይታ ቆሞ የታየው እርሱ ነበር። እንዲህ ብለን እንደምንዘምረው፡-

> እነሆ! በግልጽ ተመልከቱት፡
> ኃያሉ ድል ነሺ፡ እዩት
> መጋረጃውን ለሁለት ሰንጣቂ።

86 እነሆ፡ የስርየት መክደኛው፡ በጉባኤው ሁሉ ፊት በግልጽ ተሰቅሎ፡ መጥቷል። እነርሱ ግን በአንጋፎች አስተያየት ተጽኖ ስር ወደቁ...

87 አሁንም፡ ወንዶችና ሴቶች፡ እና የዚህ ጉባኤ ሹማምንቶች፡ አንድን ሰው ሳልፈራ ይህን መናገር እፈልጋለሁ። ነገር ግን፡ ወደ ዛሬው እይታ፡ ዛሬ እዚህ በተሰበሰብንበት እይታ መሰረትም፡ እነዚህ የአባቶች ትውፊቶች፡ እና የቤተ ክርስትያን አባቶች፡ አሁንም ነገሩን ከብዙ ሰዎች ሸፍነውታል እላለሁ። በትንቢት እንደተነገረው፡ መንፈሰ ቅዱስ በዚህ በመጨረሻው ዘመን መጥቶ፡ መጋረጃውም ተቀዶ ሳለ፡ ብዙዎች ሰዎች ግን ለራሳቸው እና ለአባቶች ትውፊት ለመሰቀል ይሞክራሉ። ይህ ከፍተኛ ደስታ፡ እና ሰላም፡ ቤተ ክርስቲያኗ

ያላትን ነገሮች ማየት የማይችሉትም ለዚህ ነው። ሆኖም፡ ለሚያምኑት በግልጽ የሚታይ ነው።

የዘመኑ የተሰፋ ቃል፡ የሆነውን ቃል ሰወረባቸው።

88 አሁንም፡ ትውፊቶች መጋረጃ ሠርተዋል። የተአምራት ዘመን አልፏል ይላሉ። እኔ በምኖርበት በቱክሰን፡ አሪዞና ውስጥ፡ አንድ መልካም፡ እውቀት ያለው ሰው፡ አነጋገረኝ። በራማዳ ጉባኤ ነበረኝና። እናም ጌታ ኢየሱስ ተገኝቶ ታላቅ ነገሮችን ሰላደረገበት የቢዝነስ ሜን ኮንቬንሽን ላይ እየተጫወትን ነበር። እናም ይህ ክርስቲያን፡ እንዲህ አለን… የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ጨዋ ሰው ነው፡ ወደ እኔ መጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ የሐዋርያት ዘመን ባበቃበት ወቅት፡" "የሐዋርያነት ዘመንን ለማሳየት እየሞከርክ ነው፡" አለኝ።

89 እኔም "እባክህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ የሐዋርያት ዘመን ያበቃበት ጊዜ አሳየኝ፡" አልኩት። አልኩት፦ "የሐዋርያት ዘመን የጀመረው፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ነው… ጴጥሮስም በበዓለ ሃምሳ ቀን፡ 'የተሰፋው ቃል ለእናንተ እና፡ ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው ብሏልና።' መቼ ነው ያበቃው? እግዚአብሔር አሁንም እየጠራ ከሆነ፣ የሐዋርያው ዘመን አሁንም በአገልግሎት ላይ ነው።"

90 ድሮ እንደነበረው ዛሬም ሰዎች በሽማግሌዎች ትውፊት፡ የብዙ ሰዎችን ዓይን፡ መጨፈን የሚሞክሩት እዚህ ላይ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ለምን ሐሴት እንደሚያደርግ እና እንደሚደሰት ማየት ተሰኗችኋል። እነዚህ ኮንቬንሽኖችም—ለሌሎች ሰዎች፡እንግዳ ናቸው፡ እብደት ናቸው፡ ምክንያቱ እነዚያን እሰራቶችን በጣጥሰው በማየታቸው ነው። እነዚያን መጋረጃዎች ጥሰው፡ በህዝብ ሁሉ ፊት የተገለጠውን፡ የዚህ ዘመን ተሰፋ ቃል ወደሚያዩበት ወደ እግዚአብሔር ህልውና ይገባሉ። እግዚአብሔር የገባውን ቃል ያያሉ።

91 በኢዩኤል 2፡28 ላይ፣ ያም፡ "በዚህ የመጨረሻ ቀናት፡ በመጨረሻው ቀን በህዝቡ ላይ **የሚፈስ** የኋለኛው ዝናብ ይኖራል።" የግሪክኛ ቃሉ **ኬኖስ** ይመስለኛል፡ ትርጉሙም እራሱን "ባዶ ማድረግ" ማለት ነው። ነገር ግን በሰው ውስጥ የነበረው ነገር፡ ፈጽሞ እሰኪጠፋ ድረስ ባዶ አደረገው፡ እንደምንለው አይነት አይደለም። እራሱን ግን፡ ፈጽሞ አፈሰሰ።

92 **ኤን ሞርፌው**፡ ለወጠ። እራሱን—ድሮ ከነበረበት፡ አሁን ወዳለበት መልክ፡ ቀየረ። ባህሪውን ግን በፍጹም አይለውጥም። በበዓለ ሃምሳ ቀን ግን፡ ራሱን የሰው ልጅ ከመሆን፡ ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ለወጠው። **ከህዝቡ** ጋር፡ መጣ ሳይሆን። **ወደ** ህዝቡ መጣ፡ እያችሁ፡ ያው አምላክ፡ በዚህ ታላቅ ዘመን ላይ፡ አገልግሎቱን ለመፈጸም መጣ።

93 በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ተንብዮአል፦ "ቀንም የማይሆን ሌሊትም የማይሆን አንድ ቀን ይመጣል፡ ሲመሽ ግን ብርሃን ይሆናል።" አሁን፡ ፀሀይ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በምስራቅ ወጥታ ወደ ምዕራብ ትጠልቃለች። ጸሐይዋ ግን፡ ሁልጊዜ ያቺት ጸሐይ ናት። አሁን፡ ጊዜው፡ ወልድ፡ ኤስ-ኦ-ኤን፡ እራሱን ለእስራኤል፡ ለምስራቅ ህዝብ፡ በተሰፋው ቃል መገለጥ፡ የሚገለጥበት ጊዜ ነው።

94 የጨለማ ቀን አሳልፈናል። አብያተ ክርስቲያናትን እና የሐይማኖት ተቋማት ለመሥራት፡ አባል የምንሆንበት፡ እና የምንገባበት፡ ህጻናትን የምንሰምበት፡

ታላላቆችን የምንድርበት፡ የሞቱትን የምንቀብርበት፡ ቤተክርስትያን ውስጥ የምንኖርበት፡ በተሃድሶ አድራጊዎች፡ እና በሌሎች ዘመን በቂ ብርሃን ነበረን።

95 ይሁን እንጂ፡ ሲመሽ፦ "ብርሃን ይሆናል፡" "ሲመሽ፡" ብሏል። እንዲት ቃልም አትወድቅም። በበዓለ ሃምሳ ቀን እራሱን ያፈሰሰው **ኬኖሰም**፡ ኤሰ-ኦ-ኤን፡ ሲመሽ ያንን ነገር በድጋሚ እንደሚያደርገው፡ ቃል ገብቷል። አያችሁ? እንደ ተሰፋው ቃል መሰረት ነው።

96 ሁለቱ ምልክቶች አንድ ላይ ግጠሟቸው። ከዛ የሚሆነውን ጠብቁ፡ ተሰፋ ቃሉንም መርምሩ፡ ከዛ በኋላ ያለንበትን ታያላችሁ። ነገሩን አንድ ላይ አጋጥሙት። የዚህን ታላቅ እና ኃያል ሰው መገለጥ ማየት ትችላላችሁ። በትንቢት የተነገሩትን እነዚን ታላላቅ ነገሮች እንዲያዩ፡ ዛሬም፡ ትውፊቶች የሕዝቡን አይን አሳውረዋል።

97 ሙሴ፡ እሳት ከነበረበት፡ ከተራራው በወጣ ጊዜ፡ ምሳሌው እንዴት ያማረ ነው!

98 ሙሴ ወደ ግብፅ ወርዶ እግዚአብሔር አምላክ "እኔ ነኝ" ተብሎ በሚታወቀው በእግዚአብሔር ሰም እንደተገናኘው ለቤተ ክርሰቲያን አባቶች ነግሮ ነበር። ሰሙ "ነበርኩ፡ እኖራለሁ" አይደለም፡ አሁናዊ ነው። ሁሌም ያው የሆነው፡ "እኔ ነኝ፡" የሆነው፡ ትናንትትናም፣ ዛሬ፣ እሰከ ለዘለአለም ድረሰ ያው ነው። አሁናዊ ጊዜ ነው። "ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ትናንትትናም፣ ዛሬም፣ እሰከ ለዘላለምም ድረሰ ያው ነው፡" ከሚለው... ከዕብራውያን 13፡8 ጋር አንድ ነው።

99 በትንቢት የተነገረው ቃል አሁንም ራሱ ነው። ጉባኤውም፡ ከቃሉ ጋር፡ ከዘመኑ ልምምድ ጋር፡ መጋጠም ይኖርበታል። ተሐድሶ አድራጊዎቹ ነበራቸው፡ ኦህ፡ ይህ ዘመን ግን ሌላ ነው። እኛ በየትኛው ዘመን እየኖርን እንዳለን ተመልከቱ። እርሱ ወደ ምድር በመጣበት ዘመን፡ እንደ ሙሴ ወይም ሌሎች ነብያት፡ በመጡበት—አመጣጥ፡ ሊመጣ እንደማይችል፡ በትንቢት አልተነገረም ነበር። በዚህ የመጨረሻ ዘመንም፣ በዚህ መንገድ እንደሚመጣ በትንቢት ተነግሯል። ሉተር በመጣበት ሪቫይቫል መልክ ሊመጣ አይችልም። ዌሰሊ በመጣበት ሪቫይቫል መልክ ሊመጣ አይችልም። ጊዜው የማቃናት ወቅት ነውና። ጊዜው ወደ ዋናው የልጅ ብርሃን መመለሰ ያለበት ወቅት ነው፡ ወደ ኦሪጂናሉ።

100 ኦህ፡ በዚያ ላይ ቅዱሳን ቃላት ማሰቀመጥ፡ እንዴት እንደምንችል! እናንተ በየትኛውም ክፍለ ዓለም ያላችሁ፡ የሰነ መለኮት ምሁራን ሆይ፡ ይህ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ። ቃል ኪዳን ነውና። ህዝቡን እንግዳ የሚያደርገው ያ ነው። እናንተ እብደት ብላችሁ የምትጠሩት፡ እነርሱን እንዲህ የሚያሰደርጋቸው ይህ ነው። ምክንያቱ... በትውፊቶች፡ በመጋረጃ ከተሸፈነበት፡ ተከፍቶ... በግልጽ ማየት ሰለቻሉ ነው። እሱ ትናንትትናና፡ ዛሬ፡ እሰከ ለዘላለም ድረሰ ያው ነው። አያችሁ? የእግዚአብሔር—የተሰፋው ቃሉ ነውና፡ ልንቃወመው አይቻለንም፡ ቅዱሳን ቃላት ፈጽመው አይወድቁምና። አዎን። ራሱን ባዶ አድርጎ ወደ ሕዝቡ ወርዶ ነበርና። ይህም አሰቀድሞ የገባው የተሰፋ ቃል ነው። ደግሞ ትናንትትናና፣ ዛሬ፣ እሰከ ለዘላለም ድረሰ ያው ነው።

101 ሙሴ፡ ወደ ግብጽ ወርዶ ይህ ነገር ካሰታወቃቸው በኋላ፡ በዛው በእሳት አምዱ መልክ፡ ወደ ሲና ተራራ ወርዶ፡ ተራራውን በእሳት እንዲቃጠል

በማድረግ፡ መልእክቱ ትክክል መሆኑ፡ አብ ራሱ አረጋገጠለት። የተሰፋውን ቃል የሰጠው እርሱ፡ ከቃሉ ጋር አመጣው። አስተውለነዋል? ትዕዛዛትን ተቀበለ። ትዕዛዛቱንም፡ ለመቀበል... ትዕዛዛቱንም ቃል ነበሩና። ቃሉ ወደ ህዝብ ገና አልወረደም ነበር። ስለዚህ፡ ቃል ሁሌ ወደ ነብይ ይመጣል፡ እርሱም የዘመኑ ነብዩ ነበርና።

102 ማለት፡ ኢየሱስ ቃል እንደ ነበረ ሁሉ። ዮሐንስም ነብይ ነበር። ኢየሱስም በውኃው ዘንድ፡ ወደ እርሱ መጣ፡ ምክንያቱ ቃሉ ሁልጊዜ፡ ወደ ነቢዩ ያለማቋረጥ ስለሚመጣ ነው። አያችሁ? ቃል እሱ ዘንድ መጣ።

103 ስለዚህ፡ ሙሴም፡ ትእዛዛቱ፡ ቃሉ ወደ እርሱ ዘንድ መጣ። እርሱም ተቀበለ። አሁን፡ ለምን? ቃሉ ከመሰጠቱ እና ከመገለጡ በፊት፡ ቃሉ በሙላት ስላልተገለጠ፡ ሙሴ ፊቱን መሸፈን ነበረበት። አንድ ነገር እንደተከሰተ አውቀዋል፡ ምን እንደሆነ ግን አላውቁም፡ ጩኸቱ ነጎድጓዱ። “እግዚአብሔር ሳይሆን፡ ሙሴ ይናገር፡” እስከሚሉ ድረስ ነበር።

104 እግዚአብሔርም፦ “ደህና፡ ይሁን። ከእንግዲህ፡ ከዚህ በኋላ በዚህ መልክ አልታይም። ነቢይን ግን እልክላቸዋለሁ። እኔም በሱ... በራሴ ነብይ እናገራቸዋለሁ” አለ።

105 እንግዲህ፡ ሙሴ፡ ከፍጥረታዊ ሕግ ጋር፣ (ጳውሎስ፡ በሁለተኛው ቆሮንቶስ ላይ፡ እንደ ከገለጠልን)፣ ፊቱን ፍጥረታዊውን መሸፈን ከነበረበት፣ ይልቅስ መንፈሳዊው ነገር ለማያምን ሰው ከመገለጡ በፊት እንዴት አብልጦ የተከደነ እና የከበረ ይሆንበት ይሆን! እንዴትስ አብልጠው... ሙሴ እብድ ነው ብለው አይናገሩበት። መጋረጃውን ጥሳችሁ፡ ወደ እሳቱ አምድ ለደረሳችሁ፡ በረከትን ይዛችሁ ለመጣችሁ ለእናንተስ፡ እንዲያው እንዴት አብልጠው አይናገሩባችሁ! አሁንም እናንተ ተጋርዳችኋል። ህዝቡ ሊያዩት አይችሉም። ሊረዱት አይችሉም።

106 “ፍጥረታዊው ክቡር ከሆነ፣ መንፈሳዊው ምንኛ ይበልጣል! ፍጻሜ ያለው፡ ፍጥረታዊው፡ ክቡር ከተባለ፡ ይህ ማለቂያ የሌለው፡ እንዴት አብልጦ የከበረ ይሆን!”

107 አሁንም፡ ግን፡ የተከደነ ነው። የተከደነው ለሚያምን ሳይሆን፡ ለማያምን ነው። ሊያየው አይችልም። እግዚአብሔር ራሱን ከማያምን ሰው ሁልጊዜ ይጋርዳል። ትውፊቶች ይሰውሩታል። ያኔ እንዳደረጉት፡ ዛሬም ያደርጉታል።

108 ፍጥረታዊ መጋረጃ የነበረበት፡ አሁን ያለን መንፈሳዊ መጋረጃ እርሱ ነው። እነዚህም ሁሉ በተጻፈ ቃል በነብይ ተገልጧል፡ ትንቢት ተናጋሪ፡ በጽሑፍ የነበረውን ቃል፡ ግልጽ ለማድረግ የሚመጣ ሰው ነው።

109 ቃል እንደመሆኑ መጠን ያውቁታል፡ ምን ማለት እንደሆነ ግን አያውቁትም። ሙሴ ግን አብራራው። “ትእዛዙ **ይህ** እና እንዲህ ይላሉ፡ ምክንያቱ ደግሞ **ይህ** ነው፡” አላቸው። ግልጽ አደረገው። ከመገለጡ በፊት ግን፡ የተከደነ ነበር።

110 ዛሬም፡ ያው ነው፡ ለሰዎች እስኪገለጥ እና ግልጽ እስኪሆን ድረስ፡ ለሰዎች ተጋርዶባችኋል። ቃል የሆነው፡ ኃያሉ አምላክ፡ እግዚአብሔር፡ በሰው ሥጋ ተጋረደ። አስተውሉ። አሁን ከማያምኑ ተሰውሮ፡ ለአማኞች ግን እንደተገለጠ አውቀናል።

111 አስተውሉ፡ ሙሴ ወደዚህ የእሳት ዓምድ ብቻውን ይገባ ነበር። ማንም ከእርሱ ጋር መሄድ አይችልም ነበር። ይህ ማለት... ለእኛ... ምን ትርጉም ይናገራል? የጴንጤቆስጤ ቡድንን በመቀላቀል ወደዚህ መግባት እንደማትችሉ ያሳያል። አያችሁ? በጭራሽ ለቡድን ገልጾት አያውቅም። ለግለሰብ ገለጸው። ዛሬም ያው ነው። "እኔ—የዚች ቤተ ክርስቲያን አባል ነኝ። እኔ—**የዚያ** አባል ነኝ፡" ትላላችሁ። ይህ ግን አይሰራም። አያችሁ?

112 ሙሴን ለመከተል የሚሞክር ሁሉ፣ እሱን ለማስመሰል መሞክር፡ ሞት ነበር። ዛሬም ያው ነው፡ ለማስመሰል መሞከር፡ መንፈሳዊ ሞት ነው። ነገሩ እንዲህ ነው...

113 ዛሬ ምሽት፡ እንድየነው፡ በዚህ ጊዜ በቡድኖቹ መካከል ያደገ፡ ሰጋው ንጽጽሮች አሉ፤ አንዱ መሰሎ ለመኖር ይሞክራል፡ ህይወቱ ግን ሌላ ነው፤ ይጠጣል፣ ያጨሳል፣ ሴቶችም በተመቻቸው... በጣም በፈለጉት መንገድ ይኖራሉ፣ እንደ ዓለማውያን፡ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው፡ ቴሌቪዥን እና የዓለም ነገሮችን ያያሉ፣ በዚህ ሁሉ ግን ራሳቸውን ጴንጤ ነን ይላሉ። እውነተኛ ለመምሰል ሙከራ ነው። ለእነርሱ፡ ገና አልተገለጠላቸውም። ሲገለጥ ግን፡ ልዩ ነው፡ በሱ መኖር ስትጀምሩ ከውስጣችሁ ነቅሎ የሚያወጣው ነገር አለው። ከዛ መጋረጃ ትሆናላችሁ። በ... በቃ አይሠራም። ማስመሰል ሞት ነበር።

114 የሙሴ መጋረጃ፡ ሙሴ ለሕዝቡ ሕያው ቃል ነበር። በዚህ ዘመንም፡ የተሸፈኑ ሰዎች እንዲሁ ናቸው። "በሰው ሁሉ እንዲነበቡ፡ የተጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው።" **አዲስ** ደብዳቤዎች ሳይሆኑ፡ አስቀድሞ የተጻፈ፡ አሁን ግን የተገለጠ ደብዳቤ ናቸው። እነዚህ—ማለት እግዚአብሔር መንፈሱን፡ በሰጋ ለባሽ ሁሉ ላይ ማፍሰሱን፡ ቃሉን እና፡ የዚህ ዘመን ተሰፋ ቃል አምነው፡ የተጻፉ ደብዳቤዎች የሆኑ ናቸው። ስለዚህ አንድ ሰው ይህን ነገር በሰጋ ማስመሰል ቢሞክር፡ ወደራሱ ተኮሰ። ህይወታችሁ ማንነታችሁን ያሳያል።

115 አንድ ጊዜ አንድ ወጣት ሰው ነበር፡ እና አንዳንድ ችግር ውስጥ ገባ። ጥሩ ልጅ ነበር፡ ግን—ፍርድ ቤት ቀረበ። ዳኛውም "ጥፋተኛ ሆነህ አግኝቼሃለሁ። የእድሜ ልክ እስራት ፈርጄብሃለሁ፡" አለው።

116 ወጣቱም፡- "የራሴን ጉዳይ በራሴ እከራከራለሁ።" "የህይወት መዝገቤን ማየት አለብኝ፡" አለ።

117 እርሱም "መዝገብ የለህም። የከሰስህ ራሱ መዝገብህ ነው፡" አለው።

118 ቤተ ክርስትያን እንደሚገባ ያላደገችበት ዋናው ምክንያት፡ ዛሬም ይኸው ነው። መዝገብ ነው። ህይወት ነው። እጅግ ቁርጠኞች መሆን አለብን። የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ማመን አለብን። ቃሉ እውን እስኪሆንልን ድረስ መለመን አለብን። አያችሁ? አያችሁ? ወደ ውስጥ እንዳንገባ የሚከለክል መዝገባችን ነው።

119 አንድ ቀን፡ ግን፡ በፍርድ ቤቱ ውስጥ (ከዚህ ውድቀት ማውጣት)፡ ልጁ ገንዘብ አልነበረውም። መክፈል አልቻለም። ቅጣቱ በሺዎች የሚቆጠር ዶላር ነበር። ነገር ግን ታላቅ ወንድም ነበረው እርሱም መጥቶ በሙሉ ከፈለለት።

120 እኛም፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ፡ ታላቅ ወንድማችን አለልን። ካመንን ከእርሱ ጋር ወደ መጋረጃው አብረን መግባት ከቻልን፡ እርሱ መጥቶ

ከፍሎልናል። የኛ ሙሴ፡ እሱ ነው። ኢየሱስ የዛሬው የእኛ ሙሴ ነው። ሙሴ፡ ተጋርዶ፡ የህዝቡ ህያው ቃል ነበር። ዛሬ፡ ኢየሱስ፡ ተጋርዶ፡ ማለት፡ ኢየሱስ በቤተ ክርስትያን ዘንድ፡ የህዝቡ ህያው ቃል ነው። መንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ በሰዎች ዘንድ ሆኖ፣ ቃሉን በዘመኑ ተሰፋ ቃል እየገለጠው፡ ህያው አድርጎታል። አሁንም ያው ነው።

121 አስታውሱ፡ ሙሴ ይህን ማድረጉ፡ እና ይህን መግለጡ፡ ይህም ለአለም ሁሉ ሳይሆን፡ ለዘጸአት ህዝብ፡ መውጣቱ ዘ-... ከዘጸአት ለሆነው፡ ለተለየ ወገን ገለጠው።

122 ዛሬም ደግሞ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ "መለኮታዊ ፈውስ ልክ አይደለም፡" በሚሉ ሰዎች ፊት ገለጠው። የምክር አገልግሎት እየሰጠው...

123 በቀደም ዕለት፡ እና አንድ ዶክተር፡ ስለ አንድ ሴት ደወለልኝ፡ ሞታቸውን የሚጠባበቁ፡ ኦህ፡ አምስት ሴቶች፡ አልጋ ላይ ተዘርረው ነበርና፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ፈወሳቸው። ዶክተሩ ማመን አልፈለገም። አለኝም፦ "ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ለምን፡" "ታ—ታ... ታካሚዬ ናት፡" አለኝ።

124 እኔም አልኩት፦ "ነበረች። አሁን ግን የእግዚአብሔር ናት። አ—አ፡ አሁን የእሱ ናት።" አያችሁ?

125 እግዚአብሔር፡ አሁን የምታዩት ነገር በስጋ ተሸፍነው፡ ለማስመሰል ከሚጣጣሩ፡ የቸርች አባል ለመሆን ከሚተጉ፡ ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሬስባይተሪያን ወዘተ ብቻ ሳይሆን፡ ከጴንጤቆስጤ ቸርቾች ሳይቀር ዘጸአት እየጠራ ነው። አንተና እግዚአብሔር ናችሁ። የግለሰብ ጉዳይ ነው። አንተ መግባት አለብህ፡ ቡድንህ ሳይሆን፡ ቤተ ክርስትያንህ ሳይሆን፡ ፓስተርህ ሳይሆን፡ መግባት ያለብህ አንተ ነህ።

126 ሌላም ሙሴ ሲወጣ፡ የነበረው ሌላ ባህሪ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። እሱ፡ ነብይ ሳለ፡ ያንን ይህል ታላቅ ሰው ሲሆን ሳለ፡ ቃል ይዞ በወጣ ጊዜ ግን፡ ህዝብ ሁሉ የሱን መቀየር አይተዋል። የሆነ ነገር ነክቶታል። በዘመኑ የተረጋገጠ የዘመኑ ቃል፡ ትዕዛዛት፡ ይዞ በወጣ ጊዜ፡ የተቀየረ ሰው ነበር።

127 እናንተም በዚህ አይነት ስብሰባ ከሚሳለቀው፡ በመለኩታዊ ፈውስ ከሚሰናከለው፡ የተአምራት ዘመን አልፏል ከሚለው የሰው መጋረጃ ጀርባ፡ በወጣችሁ ጊዜ እንደሱ ትሆናላችሁ። ሰዋዊው መጋረጃ፣ ባህላዊ መጋረጃ ወደ ኋላችሁ በጣላችሁ ጊዜ፡ የሆነ ነገራችሁ እንደተቀየረ ሰው ሁሉ ይገነዘባል።

128 ልክ እንደ ክቡር ወንድማችን ጂም ብራውን። ፕሪስባይቴሪያኖች በእርሱ ላይ የሆነ ነገር እንደተፈጠረ እንደሚያውቁ እገምታለሁ፣ ምክንያቱም— ከባህላዊ መጋረጃ ጀርባ ወጥቷል። በሰዎቹ ውስጥ፡ እሱን የሚሰብ፡ አንድ ነገር ስለአየ፡ ከመጋረጃው ጀርባ ወጣ።

129 ስለዚህ፡ እናንተም፡ ከመጋረጃው ጀርባ በወጣችሁ ጊዜ፡ የሆነ ነገራችሁ እንደተቀየረ ይታይ ዘንድ፡ በሰዎች ፊት ለፊት በሙላት ትገለጣላችሁ። ለማያምኑት፡ የተከደነ ቃል፡ ለሚያምኑት ግን የተገለጠ ቃል ትሆናላችሁ። "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።"

130 ያኔም፡ እግዚአብሔር ነው። በዚያ ዘመንም፡ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ ነበር። ይሄን እናምናለን። ነብይ ብቻ፡

ዝም ብሎ ሰው፡ ተራ ሰው አልነበረም። እግዚአብሔር በክርስቶስ ነበር፡ አምላክ በሰው ውስጥ ነበር፡ የመለኮት ሙላት፡ በሰው አካል ውስጥ ነበር። እግዚአብሔር በሰው ውስጥ!

131 አሁን ደግሞ እግዚአብሔር በሰዎች ውስጥ ነው፡ የመለኮቱ ሙላት የእግዚአብሔር ሙላት፡ በመላ ቤተ ክርስትያኑ ውስጥ በአካሉ፡ እራሱን እየገለጠ፡ ቃሉን እየፈጸመ ይገኛል።

132 አሁን፡ እግዚአብሔር፡ በሁሉም ዘመናት፡ በላዩ ላይ ቆዳ ደርቦ እንደነበረ አስተውለናል። ማለት፡ እግዚአብሔር፡ ከመጋረጃ ጀርባ ተደብቆ ነበር።

133 በደቡብ ውስጥ የተከሰተው—ትንሽ ታሪክ ያስታውሰኛል። አንድ የክርስቲያን ቤተሰብ ነበር። በዚህ የክርስቲያን ቤተሰብ እግዚአብሔርን አመኑ፡ እግዚአብሔርም ከችግር ሁሉ—ይጠብቀናል—ብለው አሰቡ። ልክ ነው፡ እሱ፡ ይጠብቃል። እና የሰባት ወይም የሰምንት አመት እድሜ ያለው፡ ትንሽ ልጅ ነበራቸው። በጣም የደስ ደስ ያለው ህጻን ልጅ ነው እና—ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ሄደ። ነገር ግን በዝናብ ጊዜ፡ በተለይም መብረቅ በሚበራበት ጊዜ ይፈራል።

134 ይህ ነገር፡ ለአንድ ሰው ነግሬዋለሁ፡ ነገሩ ተቆርጦለት ሰውዬው የተፈወሰ ሰው ነው። ይህ አገልጋይ ሰው "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ሰዎች አንተን አምላክ እያረጉህ ነው፡" አለኝ።

135 ሰውዬው፡ ተቺ ነው፡ ስለዚህ በቀላሉ፡ ልቋጨው ብዬ አሰብኩ። ለመጉዳት አይደለም፡ ታውቃላችሁ፡ ብቻ… ግን "ቢሆንስ፡ ከእግዚአብሔር ቃል የራቀ ነውን? " አልኩት፡ አያችሁ? "የራቀ፡ አይደለም፡" አልኩት፡ "ኢየሱስም ነብያትን 'አማልክት' ብሎ ጠርቷል። አየህ? እውነት ነው፡ 'አምላክ።'"

136 እነሱም፦ "እንግዲህ፡ እናንተ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቦታ ለመውሰድ ትጥራላችሁ።" ምንም ሰህተት የለውም። እውነቱ እሱ ነው። እውነት ነው። እግዚአብሔር ቃል እንደገባው፡ በሰጋ ተገለጠ።

137 እና ስለ ትንሹ ቤተሰብ፡ ነገርኩት። አሁን ወደ አእምሮዬ የመጣውን ይህ ትንሽ ታሪክ ነገርኩት። እና፡ አንድ ቀን ማታ ኃይለኛ ዝናብ ዘነበ፡ እና እናቱ ህጻኑን፡ "ልጄ፡ አሁን ደርብ ላይ ውጣና፡ ወደ አልጋህ ውጣና፡ ተኛ፡" አለችው።

እሱም፡ "እማዬ፣ ፈራሁ፣" አላት።

"ምንም የሚጎዳህ ነገር የለም። ወደ ላይ ሂድና እና ወደ መኝታ ውጣ።"

138 ህጻኑ ልጅ እዚያ ተኝቷል፣ መብረቁም በመስኮቶ ዙሪያ ብልጭልጭ አለ። ህጻኑም በጣም ፈርቶ፡ ጭንቅላቱን ከብርድ ልብስ ስር ቀብሮ ተጣብቋል፣ አሁንም ግን—መብረቁ ይሰማዋል፡ ማለት መብረቅ በመስኮት አልፎ ሲያንጸባርቅ ይታየዋል፣ የነጐድጓዱ—ድምፅም ሰማ። ስለዚህ "እማዬ!" አለ፡

እርሰዋም "ምን ፈለግክ፡ ጁኒየር? " አለችው፤

"ወደዚህ ነይ ከኔ ጋር ተኚ፡" አላት።

139 እንደ ማንኛውም ጥሩና ታማኝ እናት፡ ደረጃዎቹ ወጣችና። ወደ ላይ መጥታ፡ ህጻኑ ልጇ በክንዷ አቀፈችው። እርሰዋም "ልጄ፡ እኔ እናትህ የምነግርህ ነገር አለኝ፡" አለችው።

"እሺ፡ ማማ፡" አላት።

140 እርሰዋም አለችው፦ "አሁን ይህ ነገር እንዳትረሳ። ወደ ቤተ ክርስትያን፡ ሳናቋርጥ እንሄዳለን። መጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን። እንጸልያለን። ክርስትያን ቤተሰብ ነን። በእግዚአብሔር እናምናለን።" እና "ዝናብም ወጀቡም ይምጣ፡ እግዚአብሔር ጠባቂያችን እንደሆነ እናምናለን፡" አለችው።

141 እርሱም አላት፦ "ማማ፡ ይህን ሁሉ ነገር እኔም አምናለሁ። ነገር ግን፡" አላት፦ "መብረቁ እጅግ ሲቀርብ፡" "ስጋ የለበሰ አ—አምላክ እፈልጋለሁ፡" አላት።

142 ስለዚህ እኔ—እንደማስበው፡ ህጻኑ ብቻ ሳይሆን፡ ሁላችንም እንደዚያ ይሰማናል። ተሰብሰበን፡ አንዱ ስለሌላው ሰንጸልይ፡ እግዚአብሔር ስጋ ለብሶ።

143 ከዚህ እንደምንረዳው አምላክ ከጥንት ጀምሮ ስጋ የለበሰ መሆኑ እንገነዘባለን። ሙሴም ባየው ጊዜ፡ እንደ ሰው፡ የሰው ቁርበት ነበረበት። እግዚአብሔር ከመጋረጃው በኋላ በነበረበት ጊዜ፡ ቁርበት ለብሶ ነበር። ዛሬም፡ ይህ እግዚአብሔር፡ በቤተ ክርስትያኑ፡ ቁርበት ለብሶ በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ በመጋረጃ ውስጥ ይገኛል። ዛሬ ማታም ያው አምላክ ነው። ያንን ተረድተናል።

144 አሁንም፡ እንደ በፊቱ ሁሉ፡ ትውፊቶቹን የሚይዘው የቁርበት መሸፈኛውን ነው። ሰዎቹን እንዲህ እንዲያደርጉ ያደረጋቸው እግዚአብሔር መሆኑን ማመን አይችሉም። አያችሁ? እግዚአብሔር በቤተ ክርስትያኑ ውስጥ፡ ቁርበት ለብሶ፡ በስጋ ላይ ስለተጋረደ ነው። ትክክል ነው። ከማያምኑ ተሰውሮ፡ ለአማኞች ተገልጦ ይኖራል። የሰ፡ ሰር።

145 እንግዲህ፡ የትውፊታቸው መጋረጃ፡ የአባቶቻቸው እና የቃሉ ትውፊቶች፡ ሲገፈፉ፡ አዎን፡ እርግጥ፡ ዛሬ፡ በሰው ሰጋ የተጋረደ አምላክ ሆኖ፡ በግልጽ እይታ፡ እርሱን እናየዋለን። ዕብራውያን 1 ላይ ተናግሯል።

146 ደግሞም ኦሪት ዘፍጥረት 18 ላይ። እግዚአብሔር ቆሞ፡ ከአብራሃም ጋር፡ ሲነጋገር፡ ሲበላ ሰው ነበር፡ ታስታውሳላችሁ፡ ሣራም ከኋላው ባለው ድንኳን ውስጥ ሆና ያደረገችው ነገር ሁሉ ነገራት።

147 ኢየሱስም አለ፦ "በሰዶም ዘመን እንደ ሆነ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል።" መለኮት ዳግመኛ የሰው ሰጋ ለበሰ! አሁን ኢየሱስ፦ "የእግዚአብሔር ልጅ ሲገለጥ፡" እንዳላለ፡ አስታውሱ። በሉቃስ ምዕራፍ 17፡ ከቁጥር፡ 20ኛው፡ እና 21ኛው፡ እዚያ አካባቢ ይመስለኛል፡ "የሰው ልጅ በሚገለጥበት ጊዜ፡" ብሏል። የሰው ልጅ፡ በ—በ—በቤተ ክርስትያን ውስጥ፡ እንደገና በሰው ልጆች ውስጥ ተገለጠ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ሳይሆን፡ የሰው ልጅ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ እንደገና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ተመለሰ። በእግዚአብሔር ተሰፋ ቃላት ውስጥ ቃል ተገብቶለት እናገኘዋለን።

148 ሌላም በብሉይ ኪዳን ውስጥ፡ እናገኘዋለን። በዘፀአት ውስጥ፡ ቃላቶቹ ጽፌ ይዣለሁ። እነዚያ፡ የአቆሰጣ ቁርበቶች፡ ስራቸው ምን ነበር? የእግዚአብሔርን ክብር ከሕዝቡ መሰወር። በአቆሰጣ ቆዳዎች፡ በቁርበት ውስጥ ስለተሸፈነ፡ ሰዎች ሊያዩት አልቻሉም። በቆዳው... የእግዚአብሔር ክብር ከቆዳው በስተጀርባ ነበር።

149 አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር ክብር በቆዳዎቻችሁ በስተጀርባ ነው። አዎን። ትውፊቶች ሊያዩት አይችሉም። ቃሉ በነበረበት፡ በመጋረጃው ውስጥ ነው።

150 ያኔ በአቆስጣው ቆዳ፡ ከቆዳው ውስጥ የነበረ ነገር ምንድን ነበር?

151 ይህም፦ "እንወደው ዘንድ ደም ግባት የለውም ተባለለት። ሥጋ ሆኖ በመካከላችን ባደረ ጊዜም፡ እንወደው ዘንድ ደም ግባት አልነበረውም።"

152 ዛሬም ያው ነው። በወንድም በሴትም፡ ይወደዱ ዘንድ ምንም አይነት ደም ግባት የላቸውም። ከበስተጀርባ ያለው ነገር ይህ ነው። ይኸው ነው። "ተወው፡" "ያ ሰው፡ አውቀዋለሁ ሰካራም ነበረ። **እንዲህ** ያደርግ ነበር፡" ትላላችሁ። ምን እንደነበረ ግድ አይለኝም። ከቆዳው በስተጀርባ የተደበቀው ነገር ምንድን ነው? አስፈላጊው ነገር፡ በስተጀርባው ምን አለ ነው። ህዝቡ፡ የታወረው ለዚህ ነው። ቆዳው ህዝቡን አሳወራቸው። አያችሁ? እንዲህ ይላሉ፦ "ያቺ ሴት እንዲህ ስታደርግ አስታውሳለሁ።" ድሮ ያደረገችው አውቃለሁ፡ አሁንስ? አያችሁ?

153 አስቀድመው፡ አቆስጣው ላይ የነበሩት እነዚያ ቆዳዎች፡ አሁን ግን የእግዚአብሄርን ክብር ሰወሩ፡ ከኋላቸው ቤቱ ሰራባቸው። ድሮ እንስሳው ላይ ነበሩ፡ አሁን ግን የእግዚአብሄርን ክብር መኖርያ ሆኑ።

154 ዛሬ ማታ፡ እናንተም እግዚአብሔር የሚኖርባቸው የሰው ልጆች፡ የእግዚአብሔር መኖርያ ለመሆን፡ ቆዳችሁ መቀየር ይችላል።

155 ተመልከቱ። በጥንቱ የአቆስጣ ቆዳዎች፡ በስተጀርባ፡ መርምረን እንዳየናቸው... በውስጠኛው ክፍሉ ቃል ነበር። ቃሉ፡ እና፡ ህብስቱም ነበሩ። ታቦቱ የተረጨ ነው። እሱ ምንድነው? የአርያም ክብር በዚያ ነበረበት።

156 ቃል ዘር ነው፡ ዘር ደግሞ፡ ጸሐይ ካላገኘው በቀር-... ፍሬ ማፍራት አይችልም። ስለዚህ ዘሩ ያፈራ ዘንድ፡ ያብብ ዘንድ ወልድ በላዩ ላይ ሊወርድ ያስፈልጋል። ብቸኛው መንገዱ ይህ ነው። ቃሉን ተቀበሉ፡ አያችሁ፡ የእግዚ አብሔርን ቃል በልባችሁ ውስጥ ይዛችሁ፡ ወደ አርያም ክብር ቅረቡ። ስትቀርቡ፡ ህብስተ መና ያፈራል፡ ይህም ለተለየ ህዝብ ብቻ የሚሰጥ ህብስት ነው። ሊበሉት የሚገባቸው፡ እና ሊበሉት የሚፈቀድላቸው ብቸኛ ሰዎች፡ የሚያውቁት እና የተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። አያችሁ፡ ጳውሎስ ሲናገር፡ በስተመጨረሻ፡ ወደ ዋናው ክብር እስክንደርስ። "ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን ይላል።"

157 እንደ የማለዳ ዘር ክብር ነው። የአበባው ዘር፡ መሬት ውስጥ ይወድቃል። የበቆሎ ዘር መሬት ውስጥ ይወድቃል። የመጀመሪያው ነገር ምንድን ነው? ወደ ላይ ይወጣል፡ ይንሽ ያጎነቍላል። ከዛ ወደ ዝራረት ያድጋል። ከዝራረት፡ ወደ መጀመርያው፡ ሰብል ይመለሳል።

158 እንግዲህ፡ ቤተ ክርስትያን ያደገችውም በዚህ ነው። ከሉተር ተነስታ፡ ዌስሊ፡ አሁን ደግሞ ወደ ዋናው ሰብል፡ ወደ ዋናው ክብር፡ መጀመርያ ወደነበረው ክብር ተመልሳለች። ከክብር ወደ ክብር በመለወጥ፡ በምስራቅ የተነሣው ልጅ፡ በምዕራብ ያንኑ የሚገልጥ ልጅ ያው ነው። ከአረማውያን፡ ወደ ሉተር ተለወጠ፡ ከሉተር፡ ወደ ዌስሊ፡ ከዌስሊ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ ወጣ፤ ከክብር ወደ ክብር እየተቀየረ፡ የተደበቀውን መና፡ እያፈራ ነው።

159 እና አሁን እሱን ወደ ነበረበት፡ ወደ መጀመርያው አገልግሎቱ፡ ወደ ኃይል፡ ወደ ኢየሱስ፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ፡ ለመመለስ የበሰለ ሆኗል። በጰንጠቆስጤ ቀን የወረደው እርሱ፡ ለክብር፡ ከክብር ወደ ክብር እየተገለጠ ያለው ያው መንፈስ ቅዱስ እሱ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ በተመሳሳይ ምልክት፡ ተመሳሳይ ድንቆች፡ ተመሳሳይ ጥምቀት፡ ተመሳሳይ አይነት ህዝብ፡ ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው፡ ተመሳሳይ ኃይል፡ በተመሳሳይ ስሜት፡ ወደ መጀመሪያው ዘሩ ተመልሷል። ከክብር ወደ ክብር ነው። ከዚህ በኋላ የሚቀጥለው፡- "ከዚህ ክብር ተለውጠን፡ እሱን ወደምናይበት፡ እንደ ገዛ አካሉ ክቡር ወደ ሆነው አካል እንለወጣለን።" አብርሃምም ይህ ራሱን አይቶታል።

160 አሁን አስተውሉ። እንዴት እንደተቀየረ ይታያል። ከቀራንዮ ጀመሮ፡ የክብሩን ተካፋዮች ለመሆን ተጋብዘናል። አሁን፡ በአንደኛ ቆሮንቶስ 12፡ "በአንድ መንፈስ ሁላችንም ተጠመቅን። ወደ አካሉ ተጠመቅን።" በአንድ "ውኃ" አይደለም። "ሁላችንም በአንድ መንፈስ፡ ተጠምቀናል።" ትክክል፤ ከዛ በኋላ፡ የአካሉ ብልቶች እንሆናለን።

161 እንዳላስረፈድኳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። [ጉባኤው፡ "አላስረፈድከንም" አሉ።—እርታዒ።] እያችሁ? ተስፋ አደርጋለሁ።

162 እና፡ ተቀናጅተው እንደሚጫወቱት ልዩ የሲምፎኒ፡ ወይም ጥሩ ድራማን እንደመተወን ነው።

163 ስለ ሲምፎኒ ወይም ድራማ ብዙ እውቀት የለኝም። ጨዋታውን ግን አይቼዋለሁ… ልጄ እና ሌሎቹ የተሳተፉበትን፡ ስለ **ካርሜን** ተናግሬ ነበር። እነሱም **በካርሜን**—በዚህ በሲምፎኒው፡ይጫወቱት ነበር። ተውኔቱን ይጫወቱታል። ሙዚቃውም እ—እ—እንደ ተውኔቱ ተመሳሳይ ነበር።

164 በመንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ስትጠመቁም፡ እንደዚህ ትሆናላችሁ።

165 መቼም፡ አሁን፡ ብዙዎቻችሁ አሁን፣ ታላቁን የሩስያ አቀናባሪ የጻፈው ታሪክ **ፒተር እና ተኩላ** አንብባችኋል ሰምታችኋል። በጻናጽል እና በሁሉም ነገር፡ እንዴት እርገው እንደተወኑት። ታሪኩን የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ከወረቀት ላይ እያነበበ ነው እና ያንን ሲምፎኒ መስማት ይችላል፡ እያንዳንዱን ለውጥ ያውቁታል፡ ድራማው፡ እንዴት እንደሚተወን፡ አጨዋወቱ ሁሉ ይገባቸዋል። **እዚህ** ጋር አይተው፡ ለውጡ ማየት ይችላሉ።

166 አሁን፡ ግን፡ አቀናባሪው—አንዳች ነገር ከጻፈ በኋላ፡ ተውኔቱ ግን በተጻፈበት መንገድ ሳይሆን ሲቀርስ? ያኔ የሆነ ክፍተት እንዳለ ይገባናል። ስንመለከታቸው፡ የጎደለ ነገር አለ። አቀናባሪው ጽፎ ሰርቶ አዘጋጅቶታል፡ ሲምፎኒው ሲጫወቱት ግን፡ የተሳሳተ ቁልፍ ይጫናል። የሆነ ችግር አለ። ዳይሬክተሩ የተሳሳተ እንቅስቃሴ ሰጥቷቸዋል። እያችሁ?

167 ሉተራን ወንድሞቼ፡ መጥምቃውያን ወንድሞቼ፡ የጴንጤቆስጤ ወንድሞቼ፡ በዚህ ዘመን ያለው ችግር ይህ ነው። ከተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት የመጣችሁ ወንድሞቼ ሁሉ፡ ችግሩ ይኸው ነው። እያችሁ? የነ ሉተር፡ የነ ዌስሊ፡ እና ሌሎች ዘመን ኖታ ለመጫወት ትሞክራላችሁ በርግጥ ግን፡ የሙዚቃው ደብተር፡ ዘመኑ ሌላ መሆኑ ያሳያል። እያችሁ? እያችሁ? እያችሁ? እኛ በሉተር ብርሃን ውስጥ መኖር አንችልም፡ ተሐድሶ አራማጅ ነበርና። ድርሻውን—

እናደንቃለን፡ ጨዋታው ግን አልፈነዋል። አሁን **እዚህ** ከመጽሐፉ ጀርባ ደርሰናል። አያችሁ? እንደዚያ መጫወት አን—አንችልም።

168 ወንድሞቼ ሆይ፡ አሁን ይሄን መተግበር የምትችሉበት፡ ብቸኛው መንገድ፡ ይህ ነው። በዓለም ያላችሁ፡ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወንድሞች ሆይ፡ እኔ እላለሁ፡ ዳይሬክተሩ—ሊወጣባት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ አንድ ናት። አቀናባሪውን የገባበት ተመሳሳይ መንፈስ ውስጥ መግባት አለበት፡ ያኔ አግኝቷታል። ቤተ ክርስቲያንም ሲምፎኒው እራሱ፡ ቤተ ክርስትያን፡ እና ኮምፖዘሩ እና ዳይሬክተሩ፡ በኮምፖዘሩ መንፈስ ውስጥ ሲገቡ፡ አለም እነዚህን ምልክቶች፡ እና ድንቆች፡ የምትመለከትበት ጊዜ ነው።

169 ከዚያም "የተአምራት ዘመን አልፏል" ሲሉ፤ ትክክለኛውን ኖታ አይመታም።

170 በትክክለኛ ቅኝት ሲቃኝ ግን፡ መንፈሱም ትክክል ሲሆን፡ የአቀናባሪው መንፈስ እስኪወርድ ድረስ፡ ምን ታደርጋላችሁ? አሜን። "የተአምራት ዘመን አላለፈም፡" ስትሉ፤ ሲምፎኒው "አሜን!" ብሎ ይጮኻል፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡" ብለን ስንጫወት፤ ሲምፎኒው፡ "አሜን!" ብሎ ይጮኻል፡ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ ከወረደ በኋላ ኃይልን ትቀበላላችሁ።" ሲምፎኒው "አሜን!" አሁን አገኘሁት ይላል! ከዚያ ወዲያ በግምት መስራት ይቀራል። መላው ሲምፎኒ ከቃሉ ጋር የሚስማማ ይሆናል። ይቀጣላል... [ወንድም ብራንሃም እጆቹን አጨበጨበ—አርታዒ።] ይኸው ነው። ኦ! ድንቅ ነገር ነው። ዳይሬክተሩ እና አቀናባሪው በአንድ መንፈስ ውስጥ መሆን አለባቸው። ሙዚቀኞቹም በደንብ ለመተወን፡ በአንድ መንፈስ መሆን አለባቸው። ከዛ በኋላ ዓለም ምን ተፈጠረ ብላ ትገረማለች።

171 ስለ ኮሙኒዝም፡ ስለ ኢንተግሬሽኑ እና ስለ ሌላው ሁሉ፡ ስለ መለያየት ሲያወሩ፡ ያጥወለውለኛል። አቤቱ፡ ማረን! የጌታ መምጣት በደጅ ሲቃረብ፡ እንዲህ ያለ፡ ትርጉም አልባ ነገሮች መብዛት፡ የሆነ ችግር አለ። ስለ ዳይረክተሩ እፈራለሁ... ዳይሬክተሮቹ የኮምፖዘሩ መንፈስ ያገኛቸው አይመስለኝም።

172 የኮምፖዘሩ መንፈስ ሲያገኘን፡ ኦሪጂናሉ ኃይል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፦ "የጥንት ሰዎች ይህንን መጽሐፍ ቅዱስ ለመጻፍ በመንፈስ ቅዱስ መነሳሳታቸው፡" ይናገራልና ልክ እንደ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እና አማኝ አንድ እንደሚሆኑ ሁለቱ በአንድ መንፈስ ውስጥ ናቸውና፡ የተቀደደው የቻይናዊ ወረቀቶች አንድ ሲሆኑ ታያላችሁ። ሁለቱ አንድ ናቸው። በቀጥታ አንድ በመስመር ይጋጠማሉ። እኛ ዛሬ የሚያስፈልገን ነገር፡ ወደ ቃሉ የሚያመላክቱን፡ እንደተነገረውም የሚያምኑ፡ ዳይሬክተሮችን ነው፡ በትክክል። ከዚያም እግዚአብሔርን፡ እራሱን ታዩታላችሁ። መገለጡ ይኸ ነው። ድራማው እውን ሆነ።

173 ዛሬ ዛሬ፡ እንዲህ ይላሉ፦ "እንግዲህ፡ ቀይ ባሕርን እንደከፈለ እናውቃለን። እንዲህ **እንዲያ** አድርጓልና። ታሪካዊ አምላክ ነው። ከዕብራውያን ልጆች ጋር፡ በዚያ—በእቶን ውስጥ ነበረ።" ዛሬም ያው አምላክ ካልሆነ፡ የታሪክ አምላክ ስለሆነ፡ ምን ይጠቅማል? ሰው ከጥንት ጀምሮ ስለ ስራቸውና ወደፊት ስለ ሚያደርጋቸው ነገሮች እያሰበ አምላክን ያከብራል፡ አሁን የሚፈጸሙ ነገሮች

ግን ልብ አይልም። የሰው ባህርይ ይህ ነው። ወንድሞች ሆይ፡ ዛሬም ያው ነው። ተመሳሳይ ነገር ነው። ኦህ፡ ማይ!

174 ወደ ኋላ ተመልሰን ሲምፎኒው በትክክል ሲጫወት፡ ዓለማውያን ማየት የሚችሉትን እንመልከተው። ኢየሱስ አለ፦ "ከዚህ ምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ፡ ሰዎችን ሁሉ ወደ እኔ እስባለሁ።" እና፦ "ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው።"

175 ዳይሬክተሮች ከሙዚቀኞች እና ከአቀናባሪው ጋር በትክክለኛው መንፈስ ይግቡ፡ ሁሉም ነገር ትክክል ይሆናል። ከዚያ በኋላ፡ ከእርሱ ጋር የታወቅን እንሆናለንና፡ የግምት ስራ የለም። ዕብራውያን 13:8 "ትናንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው፡" ይላል።

176 በሐዋርያት ሥራ 2 ከእርሱ ጋር ተቆጥረናል። በአንድ ጥምቀት፣ እና በአንድ ጉዳይ፣ ከእርሱ ጋር ተቆጥሬአለሁ። ያኔ የሆነው ሁሉ እና አሁን ያለው ሁሉ፡ የነበረው እና ያለው፡ እኛም ያው ነን። በትክክል እውነት ነው።

177 እውነተኛ አሜሪካዊ መሆን ከፈለግኩ፡ ካለፈው ታሪኳ ጋር እና፡ ከአሁን ነገሯ ጋር መቆጠር አለብኝ። እውነተኛ አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ ከእሷ ጋር መቆጠር አለብኝ።

178 እውነተኛ አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ እንግዲያውስ በፕሊማውዝ ሮክ ላይ ደረስኩ። አሜን። አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ አርፋለሁ። እናንተም እንዲሁ፡ ከፕሊግሪም አባቶች ጋር በፕሊማውዝ ሮክ ላይ ደርሳችኋል። በፕሊማውዝ ሮክ፡ በደረሱ ጊዜ፡ አብሬአቸው በዚያ ነበርኩ፡ እናንተም፡ ሁላችሁም እንዲሁ ነበራችሁ።

179 ከአደጋ ተጠንቀቁ ብዬ ለማሳሰብ፡ ከፖል ሬቨር ጋር፡ መንገድ ላይ ወጥቻለሁ። በትክክል እውነት ነው።

180 እዚሁ በቫሊ ፎርጅ በኩል፡ ከብዙ ወታደሮች ጋር፡ ግማሾቹ ጫማ የሌላቸው፡ በረዷማው ደልዌርን፡ ተሻግሬአለሁ። አስቀድሜ ከጆርጅ ዋሽንግተን ጋር ሌሊቱን ሙሉ ጸልዬአለሁ። ልቤ ራዕይ ተሞልቼ ዴልዌርን ተሻግሬአለሁ። አሜሪካዊ ነን። የሰ፡ ሰር። አዎን በፎርጅ ሸለቆ፡ በትክክል ተሻግሬአለሁ።

181 ከዋነኞቹ የምስጋና አባቶች ጋር ለምስጋና ተመልሻለሁ። እግዚአብሔርን ለማመስገን ተመልሻለሁ። እውነተኛ አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ በዚያ ጠረጴዛ ላይ ተቆጥሬአለሁ።

182 እውነተኛ አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ ከስቶንዋል ጃክሰን ጋር በቆምኩ ጊዜ በዚያ ተቆጥሬአለሁ።

183 እውነተኛ አሜሪካዊ ከሆንኩ፣ ነገሮች በዓይናችን ፊት እንዲጎተቱ እምቢ ሰንል፣ የሰ፡ ሰር፡ በቦስተን ሻይ ፓርቲ አብሬ ተቆጠርኩ። እንግዲህ፡ እውነተኛዋ አሜሪካ ነኝ። በዚያ ሁሉ እኔም ተቆጠርኩ። የሰ፡ ሰር። ኦህ፡ ማይ!

184 በጁላይ፡ 4 ቀን፡ 1776 የነፃነት ደወል ደወልኩ። እውነተኛ አሜሪካዊ ለመሆን፡ የግድ ስለነበረ። የሊበርቲ ደወል ደወልኩ ነፃ መሆናችንን አውጃለሁ።

185 ወንድም ከወንድም ጋር ሲዋጋ፡ በአብዮታዊ ነውጥ ውስጥ አብሬ ተቆጥሬአለሁ። ክብሯን መሸከም እንዳለብኝ ሁሉ ነውሯም መሸከም አለብኝ። አሜሪካዊ ከሆንኩ፡ መሆን አለብኝ። ከሷ ጋር ተቆጠርኩ። የስ፡ ስር።

186 ሊንከን ንግግሩን ባደረገበት ወቅት፡ በጌቲስበርግ አብሬ ተቆጠርኩ። የስ፡ ስር።

187 በደም በጨቀየ በወታደሮቹ አካል፡ በዌክ ደሴት ላይ ነበርኩ። ዌክ ደሴት ላይ ተነሳሁ።

በጉዋም ላይ፡ ያን ባንዲራ እንዲሰቀል ረድቻለሁ።

188 እውነተኛ አሜሪካዊ ነኝ። አሜን። እሷ የሆነችው ሁሉ፡ እኔም ነኝ፡ ኩራት ይሰማኛል። በደንብ፡ ነዋ። አሜሪካዊ ለመባል፡ አሜሪካ ያለፈችበት ሁሉ፡ አሁንም የሆነችው ሁሉ፡ እኔም ደግሞ ነኝ። እኔም ከእሷ ጋር ተቆጥሬአለሁና፡ እሷ የነበረችው ሁሉ፡ መሆን አለብኝ።

189 ተመሳሳይ ነገር ነው፣ እውነተኛ ክርስቲያን በመሆን፡ ከእሱ ጋር ትቆጠራላችሁ።

190 ከሙሴ ጋር አብሬ ሰበክሁ፡ ከኖህ ጋር አብሬ-... ሰዎች፡ ከመጪው ፍርድ አምልጠው፡ እውነተኞች ክርስትያኖች እንዲሆኑ አሰጠንቅቄአለሁ።

191 በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ ከሙሴ ጋር ነበርኩ። የእሳቱን አምድ አይቼዋለሁ። ክብሩን አይቼአለሁ። ክርስቲያን ለመሆን፡ ከሙሴ ጋር በዚያ ምድረ በዳ ነበርኩ። ክርስቲያን ለመሆን፡ እግዚአብሔር በሚታወቅበት ነገር ሁሉ መቆጠር አለብኝ። ክብሩን አይቻለሁ። ድምፁን ሰምቼአለሁ። እኔ እራሴ እዚያ ስለነበርኩ፡ የሚያርቀኝ ምክር እኔን ለመምከር አትሞክሩ። የምናገረውን አውቃለሁ። የሆነውን አይቻለሁ። የስ፡ ስር።

192 የእግዚአብሔር መንፈስ ወርዶ ውሃውን ወደ አንድ ወገን ሲከፍለው፡ በቀይ ባህር ላይ ነበርኩ፣ ዛሬ እንደሚሉት፡ በሸምበቆ ክምር በኩል ሳይሆን፡ ዘጠና-ጫማ በሚያህል ባሕር መካከል ነበር። የእግዚአብሔርን መንፈስ አይቻለሁ። ከሙሴ ጋር በደረቁ መሬት፣ ቀይ ባህርን ተሻግሬአለሁ።

193 በሲና ተራራ አጠገብ ቆሜ ነጎድጓዱና መብረቁ ሲወድቅ አየሁ። አብሬያቸውም መና በላሁ። ክከአለቱ ውኃ ጠጥቻለሁ። ዛሬም እየጠጣሁ ነኝ። ምመና-ከሚመገቡት ጋራ ተቆጥሬአለሁ። ከአለቱ ውኃ ከሚጠጡት ጋር ተቆጥሬአለሁ።

194 ኢያሱ መለከት ሲነፋ እና የኢያሪኮ ግንብ በፈረሰ ጊዜ እኔም ተቆጥሬአለሁ።

ከዳንኤል ጋር በአንበሶች ጉድጓድ ነበርኩ።

ከዕብራውያን ልጆች ጋር በሚነደው እቶን ውስጥ ነበርኩ።

በቀርሜሎስ ተራራ ላይ... ከኤልያስ ጋር ነበርኩ።

195 በተቺዎች ፊት፡ ከመጥምቁ ዮሃንስ ጋር ነበርኩ። የእግዚአብሔር መንፈስ ሲወርድ አይቻለሁ። የእግዚአብሔር ድምፅ “በእርሱ እኖር ዘንድ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡” ሲል ሰምቻለሁ። የስ፡ ስር። በትክክል ከእርሱ ጋር ተቆጠርኩ። ይህ እውነት ነው።

196 አልዓዛርን ባስነሳው ጊዜ፡ በአልዓዛር መቃብር አጠገብ በዚያ ተቆጠርኩ። በጉድጓዱ አጠገብ፡ ሐጢአቶቿን በነገራት ጊዜ፡ እኔም ተቆጠርኩ። የሰ፡ ስር።

197 በሞቱ ከእርሱ ጋር በእርግጥ ተቆጥሬአለሁ። በመጀመርያው ፋሲካም ተቆጥሬአለሁ። ክከእርሱ ጋር አብሬ ከሙታን ተነሳሁ። ከሞቱም ጋር አብሬ ተቆጠርኩ።

198 በላይኛው ክፍል ውስጥ ከመቶ ሀያዎቹ ጋር ነበርኩ። አብሬአቸው ተቆጠርኩ። ሄይ! መንፈሳዊ—ስሜት ሞላኝ። ኦህ፡ ማይ! አብሬ ተቆጥሬአለሁ። እኔም አንዱ ነኝ። ተቆጥሬአለሁ። እነሱ የነበራቸው ልምምድ ለእኔ አለኝ። እውነተኛ ክርስትያን ለመሆን፡ ነገሩ ሲፈጸም እኔም ነበርኩ። ኃይለኛው ንፋስ ሲመጣ አይቻለሁ። እኔም መሰክሬአለሁ። በተንቀሳቀሰ ጊዜ የእግዚአብሔር ኃይል ነካኝ። በልሳኖች ከሚናገሩት ጋር እኔም ነበርሁ። ቅባቱ እዚያ እንደገባ ተሰማኝ። አብሬያቸው ነበርኩ። መንፈስ ቅዱስ በልሳኖች መናገር ሲጀምር፡ ከእነሱ ጋር ተቆጥሬ ነበር።

199 በሐዋርያት ሥራ 2 ላይ ጴጥሮስ፡ በተቺዎቹ በፊትየሰበከውን ስብከት በተናገረ ጊዜ፡ ከእርሱ ጋር ነበርኩ። ከእርሱ ጋር ተቆጠርኩ። የሰ፡ ስር።

200 በሐዋርያት ሥራ 4፣ አንድ ላይ ተሰብስበው፣ የነበሩበት ቤት በተናወጠ ጊዜ፡ አብሬያቸው ነበርኩ። ከጸሎት ሰብሰባ በኋላ፣ የነበሩበት ቤት ተናወጠ። እኔም በዚያ አብሬአቸው ተቆጥሬአለሁ።

ከጳውሎስ ጋር በማርስ ሂል ሰበክሁ። የሰ፡ ስር።

201 ከዮሐንስ ጋር በፍጥሞ ደሴት ነበርሁ፡ የዳግም ምጽአቱን አይቻለሁ።

በተሃድሶው ከሉተር ጋር ነበርኩ።

202 ከእሳት ካመለጠው፡ ከእሳቱ ትሩፋት፡ ከዌስሊ ጋር አብሬው ነበርኩ፡ በአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ባነሱበት ጊዜ። አብሬው ነበርኩ።

203 ዛሬ ምሽትም፡ 1964፡ በፊላደልፊያ፡ ፔንሲልቫኒያ፡ አሁንም ከተመሳሳይ ቡድን ጋር፣ ከተመሳሳይ ልምምድ ጋር አብሬ ቆሜአለሁ። ክርስትያን ለመሆን፡ ይህ እሆን ዘንድ ያሰገድደኛል። የእግዚአብሔር ቃል በሚገለጥበት ቦታ ጸንቼ መቆጠር አለብኝ። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሚሰማው ቡድን ጋር የተቆጥረ ሰው ነኝ።

204 እሱ እንደተገለጠ ከሚያውቅ ቡድን ጋር ተቆጥሬአለሁ፣ ትናንት፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ድረሰ ያው እንደሆነ፣ ይህ አክራሪነት እንዳልሆነ ከሚያውቁት ጋር ተቆጠርኩ። "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለም ያው ነው።" ከዚ ቡድን ጋር፡ ዛሬ ማታ ተቆጠሬአለሁ። ሰለ እግዚ አብሔር ቃል፡ አሁንም መናፍቃን ከሚባሉት ጋር፡ ወግ አጥባቂዎች ከሚባሉት ጋር። ይሁን እንጂ፡- "የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አላፍርም።" እኔም አንዱ ነኝ። እንደተናገርኩት፡ በወንዶች እና በሴቶች ውስጥ፡ በሰው አምሳል የተጋረደ አምላክ፡ ከሚነበቡ ደብዳቤዎች ጋር፡ የተገለጠ ነኝ። ኦህ!

205 እግዚአብሔር በድጋሚ በራሱ **ኤን ሞርፌ**፡ ራሱን እየገለጠ፡ ራሱን ለህዝቡ አሳወቀ። ክብሩን ወደ ጎን የጣለ ታላቁ ንጉስ። "ገና ትንሽ ጊዜ አለ ከእንግዲህ ዓለም አያየኝም። ለእነርሱ እጋረድባቸዋለሁ። እናንተ ግን እስከፍጻሜው ድረስ፡

ከእናንተ ጋር፡ በእናንተም ውስጥ ስለምኖር፡ ታዩኛላችሁ፡ ከሉተር ወደ ዌስሊ፣ ከፍ ከፍ እያልኩ፣ ከክብር ወደ ክብር እለወጣለሁ። ህያው ሆኜ የምኖር ያው አምላክ ነኝ፡ ወደ ዋናው ክብር ተመልሼአለሁ።" ሃሌ ሉያ!

206 ሁሉም አይነት የሐይማኖት ተቋም መጋረጃ፡ እና ከልካይ ድምጾችን በሙሉ ሰባበረ። "ኦህ፣ ይህ አክራሪነት ነው፡" የሚሉ አይነት ድምጾች ሁሉ፡ ሰባበራቸው። ከነዚያ መጋረጃዎች፡ የሚወጡ ድምጾች፡ "ኦህ፡ እነዚህ ሰዎች እብዶች ናቸው፡" የሚሉትን ሁሉ ሰባበራቸው። አዎን፡ ሰባበረው። "ኦህ፡ አይሳካላችሁም። ተራ የመናፍቃን ስብሰብ ናችሁ።" የሚሉትን ሁሉ በዚያ ሰባበራቸው። ኦህ፡ ማይ፡ በቃሉም እንደተናገረ፡ "መለኮታዊ ፈውሰ የሚባል ነገር የለም።" የሚሉትን በዚያ ሰባበራቸው። የእግዚአብሔር ቃልን ማሸነፍ አትችሉም።

207 ዛሬ ምሽትም፡ ኃያል ድል ነሺ፡ እነሆ፡ ቆሟል፡ የሜቶዲስት፣ የባፕቲስት፣ የፕሪስባይቴሪያን፣ እና ሌላው ዓይነት መጋረጃ ሁሉ ሰባብሮ ቆሟል። እነሆ ዛሬ ማታም፡ በትውፊቶች የማይበገር ሆኖ፡ በህዝቡ መኃል ቆሟል። ሰዎች የሚፈልጉትን ይናገሩ፣ የሚፈልጉትን ያድርጉ፣ የፈለጉትን ሁሉ ይሁኑ። እግዚአብሔር ግን ያንን ድምጽ እየሰባበረ፡ መጣ።

208 አስታውሱ፡ ሰዎች እንደነገሩኝ ከሆነ፡ አውሮፕላን የድምጽ ክልከላውን ጥሶ ሲወጣ፡ ለፍጥነቱ ወሰን አይኖረውም ይባላል።

209 እውነት እላችኋለሁ፡ እናንተም "ኢየሱሰ ድሮ ነበር፡ ዛሬ የለም፡" የሚሉ ትውፊታዊ ገደቦች ስትሰባብሩ፡ ትላንትና፣ ዛሬ እና ለዘላለም ያው እንደሆነ ሲገባችሁ፣ እግዚአብሔር በዚህ ኮንቬንሽን ለሚሰራው ሰራ እና፡ ዓለም የሚያስፈልጋቸው ምን እንደሆነ፡ ማለት የዓለም ቅጣት ሳይሆን፡ በህያው አምላክ ህልውና በመንፈሰ ቅዱሰ ጥምቀት ሙላት የመጥለቅለቁ ማሳያ ገደብ አይኖረውም፡ **ኤን ሞርፌ** ራሱን በሰው ሥጋ ሸፈነ። ሃሌ ሉያ! እምናለው።

210 መጋረጃዎች ሁሉ፡ ከልካይ ነገር በሙሉ፡ የሚጋርድ ነገር ይሰባብራል! ህልውናውን ማንም አይሸፍነውም። ሰዎች በልባቸው ሲራቡ፣ ሊሰበር የተዘጋጀ መጋረጃ ከሆናችሁ። በእሱ ላይ ብቻ ልትመኩ ትችላሉ። መጋረጃ ሁሉ፡ በመንፈሰ ቅዱሱ ቀደደው!

211 እነሆ በዚህ ምሽትም፡ ኃያሉ ድል ነሺው፡ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለም ያው ሆኖ፡ እንደ ድሮው፡ በሽተኞችን እየፈወሰ፡ አማኞችን እያጠመቀ ቆሟል። ኃይል ድል ነሺ ነው። የተፈረደባቸው ሰይጣኖች ሽሽት ላይ ናቸው። የሰ፡ ሰር። እሱ ሲመጣ ሁሌም ይሸሻሉ።

212 በመጨረሻው፡ ይሄን ልበል፡ ከዚህ በፊት... ከብዙ አመታት በፊት፡ ስለ አንድ ቫዮሊኒስት፡ ያነበብኩት ታሪክ ነው። ታሪኩን፡ ብዙ ጊዜ ሰምታችሁታል። እና የሚሸጥ ያረጀ ቫዮሊን ነበረው። እና ለሆነ ነገር ስለፈለጉት መሸጥ ፈለጉ። አጫራቹ አለ፦ "**ይህን-እና-ይህን** ያክል ማን ይሰጠኛል? " ይመስለኛል ጥቂት ሳንቲሞች፡ ምናልባትም ሃምሳ ሳንቲም፡ መሰለኝ ያቀረበላቸው። "ሊሸጥ ነው አንድ፡ ሊሸጥ ነው ሁለት፡... "

213 ወድያውኑ፡ አንድ ሰው ከኋላ ተነሣ። "አንዴ ቆይ፡" አለ። ወደ ፊት ሄዶ ተቀበለው። ይህን የተጫወተው እንደሆነ እናስብ፦

በደም የተሞላ የደም ፏፏቴ አለ፤
ከአማኑኤል ደም ስር የተቀዳ፡
ሐጥያተኞች ከፏፏቴው ስር ሲወድቁ፡
የሐጥያት እድፋቸው ያስለቅቃል።

214 ዘምሮ ካስቀመምጠው በኋላ፡ ያላለቀሰ ሰው አልነበረም። ከዛ በኋላ "የሚገዛ ሰው አለ? " አላቸው፡

215 አንዱ "አምስት ሺ፡" አለ። "አስር ሺ።" ሊተመን የማይችል ሆነ። ለምንድነው? የቫዮሊኑ ባለቤት—ጥራቱን ስለገለጠላቸው።

216 አሁንም፡ ወንድሞቼ፡ እህቶቼ ሆይ፡ ይህን ቃል የጻፈ፡ የቃሉ ባለቤት፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ቀስቱን በፍቅር ያንሣና፣ በልብባችሁ ውስጥ ይሰካው።

በደም የተሞላ የደም ፏፏቴ አለ፤
ከአማኑኤል ደም ስር የተቀዳ።

217 ከዛ ሙሉ ዋጋውን ታዩታላችሁ፡ የተገለጠውን አምላክ በፊታችሁ በግልጽ ታዩታላችሁ። ይህም፡ በበዓለ ሐምሣ ቀን፡ በሰዎቹ ሁሉ ላይ ሲወርድ እንደነበረው፡ እራሱን ወደነሱ **ኬኖስ** ባደረገ "ባዶ" ባደረገ ጊዜ እንደነበረ አሁንም ያው ነው። ትክክል።

218 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ ሞክሬአለሁ። ሞካክሬአለሁ። **ይህንን፣ ያንን፣ ሌላውን** አድርጌያለሁ፡" ትላላችሁ።

219 አንድ ቀን በካርልስባድ፡ ኒው ሜክሲኮ ሰብሰባ ነበረኝ። እና ወደትልቁ ጥንታዊ የሌሊት ወፍ ዋሻ ውስጥ ወረድን። የሚያስፈራ-አይነት ነበር፡ እና ወረድን። እና—ሰውዬው፡ ወደ ታች ከወረደ በኋላ፡ መብራቱን—ድርግም አርጎ አጠፋው። ኦህ፡ ማይ፡ ምን ያህል ድቅድቅ ጨለማ እንደነበረ፡ መገነት ትችላላችሁ። ብቻ... የሚዳሰስ ጨለማ ነው።

220 ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ያልቻለችውን ቤተ ክርስቲያን፡ የምናይበት ጊዜ መድረሱን ነው፤ የጽዮን ሴቶች ልጆቻችን የምሚያደርጉትን ነገር ስታዩ፣ ይየሚያጨሱ እና የሚሰክሩ ወንድሞች ስታዩ፡ ቆሻሻ ቀልዶች—ሲያወሩ፣ በዚህ ሁሉ ደግሞ የክርስቶስን ተከታዮች ነን ይላሉ። ኦህ፡ ማይ፡ ጨለማ ነው። ድቅድቅ ጨለማ ነው።

221 የመምጣቱን ምልክት አይተናል። ከቀኑ በፊት ሁል ጊዜ ጨለማ ነውና... እንዲሁ ይሆናል። ከዚያ በኋላ ቀኑን ለማብሰር፡ እና ለማወጅ፡ መምጣቱን ለማሳየት፡ የንጋት ኮከብ ይወጣል። አስተውሉ።

222 እዚያ ውስጥ፣ ልክ ሲያጠፉት፣ አንዲት ትንሽ ልጅ ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮኸች። ሌላ ትንሽ ልጅም ከጋይዱ ጎን ቆሞ ነበርና፡ መብራቱን እንዲህ አርጎ ሲያጠፋት አስጎብኚውን አይቶት ነበር። ህጻኗ ልጅ ልትወድቅ ነበር። **ወደላይ-እና-ወደታች** እየዘለለች፡ ትጮኽ ነበር። "ኦህ! አሁን ምን እንሆናለን? ምን ተፈጠረ? ምን ተፈጠረ? "

223 ምን ብሎ እንደተናገራት ታውቃላችሁ? "አትፍሪ፡ ትንሿ እህቴ። መብራቱን ማብራት የሚችል ሰው ከዚህ አለ፡" አላት።

224 ስሚኝ፡ ታናሽ እህቴ፡ ጥቂቶች ነን እናሳ ነን ብለሽ ታስቢ ይሆናል። ግን፡ አትፍሪ። መብራቱን ማብራት የሚችል ሰው ከዚህ አለ። መንፈስ ቅዱስ ነው። ታምናላችሁ?

225 ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ስላስረፈድኳችሁ አዝናለሁ።

226 ታላቁ የሰማይ አምላክ ሆይ፣ እራስህን ገልጠህ፣ እራስህን ፈትተህ፣ እራስህን ታላቁ የክብር ንጉሥ፣ መሆንህን ስታሳውቅ፡ ዛሬ ማታ፡ እነዚህን ትንንሽ ምሳሌዎች፡ ውሰድ እና በሰዎች ልብ ውስጥ ጣላቸው። ያን የተገለጠውን፡ ወርዶ የቤተ መቅደሱን መጋረጃ የቀደደውን ከመጋረጃውም ወድያው ወጥቶ፡ በበዓለ ሐምሣው ቀን፡ እንደገና ውደ ሰዎች መጋረጃ ውስጥ የገባውን፡ ከክብር ወደ ክብር እየተሸጋገረ፡ ሳይለዋወጥ የኖረውን፡ ማየት ይሁንልን።

227 እኛም እንደ ተፈጥሮው ሁሉ ተመልሰናል፡ በትወናው፡ ከአንዱ ቤተ ክርስትያን ወደ ሌላኛው፡ ወደ ዋናው ዘር ተመልሰናል። በዚህ በመጨረሻው ዘመን፣ ቅዱን ቃላት ሁሉ ለመፈጸም፡ እነሆ፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ወደ ወረደው፡ ወደ ዋናው ነገር እንመለሳለን፡ “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡” እና፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተም ታደርጋላችሁ፡” የመሳሰሉና በቃልህ ውስጥ ቃል የገባሃቸው ሌሎች።

228 አባት ሆይ፡ ገና መጋረጃውን ያልጣሰ አንድም ሰው ቢኖር፡ ወይም መጋረጃውን ጥሶ ያለፈውን ሰው ለማስመሰል የሚሞክር ሰው ካለ፡ አባት ሆይ፡ በዚህ ምሽት ጸጋህን ስጠው። ያንን ኃያል ድል ነሺ፡ ይቅር ለማለት ጸጋ እና ኃይል ተሞልቶ፡ እዚህ ቆሞ ይዩት። ስጠን፡ አባ።

229 ጭንቅላታችንን ዝቅ እንዳደረግን፡ እንዲህ አይነት ሰዎች ካላችሁ? ስንቶች ናችሁ፡ እስኪ ልያችሁ፡ “ወንድም ብራንሃም፣ እጄን አንስቻለሁ። ጸልይልኝ”? የምትሉ፤ ጭንቅላታችሁን ዝቅ አድርጋችሁ፡ እጃችሁን ወደላይ፡ “ድል አድራጊውን በእውነት እስካይ ድረስ፡ እያንዳንዱን መጋረጃ ማለፍ እፈልጋለሁ።” እግዚያብሔር ይባርካችሁ። ማይ፡ እጆች ላይ! በረንዳው ላይ፡ በስተቀኝ በኩል? እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ከኋላ በረንዳው ላይ? እጅ ወደ ላይ… እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ቅኖች ሁኑ። በግራ በኩል? እጅ ይነሣ፡ እና እንዲህ በሉ፦ “ወንድም ብራንሃም፣ ለብዙ ዓመታት ክርስቲያን ሆኜ ሊሆን ይችላል፣ ግን፣ በእውነቱ፣ መጋረጃውን አልፌ አላውቅም። እስከ አሁን አልቻልኩም። ያኔ የነበራቸውን የለኝም።” ዛሬ፡ ያሉንን… “በእንስራ ውስጥ የተተከለች ተክል ነኝ።”

230 በእንስራ የሚበቅል አበባን ውሰዱ፡ ትንከባከቡታላችሁ፡ ታርሙታላችሁ፡ ትረጩታላችሁ፡ ታጠጡታላችሁ። በረሃ ላይ የሚበቅለውን ኦሪጂናል ተክል ግን፡ አበባው አንድ አይነት ነው፡ ይመሳሰላሉ፡ ጠብታ ውኃ የሚያጠጣው የለውም፡ ነፍሳት አያርፉበትም። ወጣ ገባ ነው። እውነተኛ ነው።

231 ክርስትናን ከክርስትና ጋር፡ ያኔ ከነበረው ጋር ማወዳደር ትችላላችሁ? ዛሬ ክርስቲያኖች የምንላቸው፡ በዓለም ዙሪያ ያሉ፡ እነዚህ ቡድኖች፡ ከበዓለ ሃምሳ በኋላ በኋላ ከነበሩት ጋር ስታስተያዩአቸው፡ ከአንዱ ቸርች ወደ ሌላው፡ እንክብካቤ እና እሹሩር የለመዳችሁ፡ እና፡ የማትወዱት አንድ ነገር ከተነገረ፡

ተነስታችሁ ትወጡ የለ? ታዲያ፡ ኦህ፡ መገመት ትችላላችሁ? በጭራሽ። ምንድነው የተፈጠረው? መባዛት ነው።

232 የሙሴን ሀውልት የፈጠረው፡ ማይክል አንጄሎ፡ የዚያን የተባዛውን በጣም በርካሽ፡ ታገኙታላችሁ። ኦሪጂናሉ፡ ግን?

233 የጌታን እራት የተሳለው ሰዕል፡ ልግዛው ብትሉ፡ ኦሪጂናል ሰዕሉ ብዙ ሚልዮን ዶላሮች እንደሚሆን እገምታለሁ። እኔ የት እንዳለ እንኳን አላውቅም። የሰዕሉ የተባዛ ሰዕል ግን በአንድ ዶላር ከሰማንያ-ሰምንት ሳንቲም ታገኙታላችሁ። ይሄን ትችላላችሁ።

234 ዛሬም እንደዛው ነው። ርካሽ ክርስቲያን፣ የተባዛ፣ የቤተክርሰቲያን-አባል ብቻ፣ በሲጋራ ወይም—በተራ መጠጥ ልትገዟቸው ትችላላችሁ። ወይም፡ ጸጉሯን ቆራርጣ፡ ከንፈሯን የምትቀባ ሴት፡ በአለም ካለው በየትኛውም አይነት ፋሽን ልትገዟት ትችላላችሁ። እውነተኛዋን መንካት ግን አትችሉም።

235 ትላንትና፡ ዛሬ፡ እሰከ ለዘላለም ድረሰ ያው ሆኖ፡ በግልጽ በሙላት አየሁት።

236 ክርሰቲያን ሆይ፡ እውነተኛ ክርሰቲያን መሆን አትፈልጉምን? እጃችሁ ያላነሳችሁ ካላችሁ፡ ለማንሳት ፈቃደኞች ትሆናላችሁን? መልካም፡ አሁን ልጸልይ ነው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ኦህ፡ እሰኪ ተመለቱት። በጣም ደሰ ይላል።

237 የሰማይ አባታችን ሆይ፦ "ቃልህ ወደ አንተ በከንቱ አይመለሰም።" ቃል የገባኸው አንተ ነህና። አንተ የተናገርከውን በመናገሬ ብቻ ተጠያቂ ነኝ። ቃላትህን እየደጋገምኩ ነው። አንተም፦ "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።" ብለህ ቃል ገብተሃል።

238 እና፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬም እናምናለን የሚሉ፡ እምነት ግን የሌላቸው፡ ብዙዎች የተባዙ መኖራቸው፡ እናውቃለን። ይታያል። ግን፡ ጌታ ሆይ፡ አንዳንድ እውነተኞችም፡ አሉ።

239 እዚህ፣ ዛሬ ማታ፣ ወንድ እና ሴት፣ ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ፣ የየትኛውም ብሄር ቢሆኑም፣ የየትኛውም ቀለም፡ የየትኛው ቤተክርሰትያን እንደሆኑ፡ አምላክ ሆይ፡ እንዲሞላቸው፡ እጸልያለሁ። ዛሬም የዚያው ኢየሱስን እውነተኛ መገለጥ፡ በጴንጤቆሰጤ ቀን እንዳደረገ ሁሉ፡ መንፈሰ ቅዱሰ ሆኖ፡ እራሱን በሚገልጥበት ዘመን፡ እሱን በመካከላችን ይዩ። አድርግልን፡ ቃላቶቹ ሲከናወኑ፡ ትንቢቶች ሲፈጸሙ ታይቷልና!

240 እሰኪ አሰተያዩአቸው፡ ዛሬ፡ በዓለም ያለችውን ቸርች፡ የዓለም አብያተ ክርሰትያናት ጉባኤን፡ እና በበዓለ ሃምሳ ቃል ኪዳን የተገባላት? በምንም፡ ማነጻጸር አይቻልም። በዚያ ቲኬት ልብሳችንም ማሳጠብ አንችልም።

241 ነገር ግን፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ ወደዚያ ምንጭ ከተመለሰን፣ የመንጻት ሂደት አለው፣ ከዚያም ልምምዳችን እና የእግዚአብሔር ቃል አንድ ይሆናሉ። ከዚያ፡ ርሰታችንን መውረሰ እንችላለን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ሰዎቹን ወደ እጅህ በማሰረክባቸው ጊዜ፡ ይህ ነገር አድርግልን። አባት ሆይ፡ ለእያንዳንዳችን፡ የሚያሰፈልገንን ሰጠን። በኢየሱሰ ሰም እንጠይቃለን። አሜን።

242 እግዚያብሔር ይባርካችሁ። ብዙ ሰዓት፡ ስለቆማችሁ፡ አብዝቼ፡ አመሰግናችኋለሁ። እና ይቅርታ አርጉልኝ አሰር ጉዳይ ለአሰር ድረሰ አቆይቻችኋለሁ። በማለዳ እስከማያችሁ ድረስ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን። አገልግሎቱን አሁን፡ ወደ ጉባኤው መሪ፡ ማስረከብ ያለብኝ ይመስለኛል።

**በፊታችን የተገለጠው ኃያል አምላክ** AMH64-0629

(The Mighty God Unveiled Before Us)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሰኞ ምሽት፡ ሰኔ 29፡ 1964፡ ለፉል ጎሰፔል ቢዝነሰ ሜንሰ ፌሎሺፕ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን፡ በፊላደልፊያ፡ ፔንሰልቬንያ ዩ.ኤስ.ኤ. ከሚገኘው ከቤሌቭዌ-ሰትራትፎርድ ሆቴል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org